# Bahir Dar University

## Motto of Bahir Dar University

"Wisdom at the Source of the Blue Nile"

"ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ"

## Vision

The vision of Bahir Dar University is to become one of the ten premier research universities in Africa by 2025.

## Mission

The mission of Bahir Dar University is to contribute substantially to the nation and beyond through high quality education, research and community services.

### Core Values

- Quality
- Discourse
- Innovation
- Integrity
- Democratic culture
- Social responsibility

---

# ናይል ጋዜጣ

በኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
የውስጥ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ክፍል
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

**የአማካሪ ቦርድ አባላት**

ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ
ዶ/ር ጌታቸው ፍስሃ
ዶ/ር ጥጋብ በዜ
ዶ/ር እንየው ታደሰ
አቶ በላይነህ ወርቁ
ወ/ሪት እንዳስ ቃሶ
አቶ ፈታሒ በቃሉ
አቶ ብሩክ ከተማ
አቶ ቴዎድሮስ ካሳዬ

**ዋና አዘጋጅ፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ም/ዋና አዘጋጆች**
ሀሰን ዑስማን
ሂሩት አድማሱ

**አርታኢዎች**
ሂሩት አድማሱ
ሰሎሞን ሙሉ
ቃለአብ ሞላ
እየሩስ ካሱ

**ግራፊክስና ሌይአውት፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ዘጋቢዎች፡-**
የማነ ገብሩ
ታድዬ አስማረ
አምሳሉ ጥላሁን
ትዕግስት ዳዊት
አበባ ሐብቴ
ሙሉጎጃም አንዷለም

**አምደኞች፡-**
ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
ፈታሒ በቃሉ
አበባው ይረጋ (ዶ/ር)
የኑስ ኑሬ
አደላች ታፈረ
ደስታ ተከስተ

**ፎቶ አንሺዎች፡-**
ታምራት አታላይ
ሙሉጌታ ዘለቀ

**የኮምፒውተር ጽሁፍ፡-**
ታሪክ ታደሰ
የሻለም መንግስቴ

**ትራንስፖርት፡-**
ማናለ ኃይሌ

**መልእክተኞች፡-**
ንብረት ታፈረ
ይርጋ ሻረው
አለምነሽ ሙሉ

ስልክ፡- +251 583206088
+251 583207023

## ርዕሰ-አንቀጽ

# በተግባቦት ስራ የዩኒቨርሲቲውን ራዕይ ለማሳካት የማህበረሰቡ ተሳትፎ ወሳኝ ነው!

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የተሰጡን ወርቃማ ግቦች ማለትም በመማር ማስተማር፣ በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎት ለማሳካት ዘርፈ ብዙ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡ እነዚህ ወርቃማ ተልዕኮዎች ያላቸው አፈፃፀም በተግባቦት ሥራ መታጀብ ይኖርባቸዋል፡፡ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከ40 ሺህ በላይ ተማሪዎች በ1ኛ፣ 2ኛ እና በ3ኛ ድግሪ የሚያስተምር ከ4000 በላይ የአካዳሚክና የአስተዳደር ሠራተኞችን ያሉበት ግዙፍ ተቋም ሲሆን በባሕር ዳር ከተማ በሁሉም አቅጣጫዎች ግቢዎችን በመክፈት ተልዕኮዎቹን ለመፈፀም እየተጋ ይገኛል፡፡ ወደፊትም ይህንኑ ሥራ አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በአዴት፣ በደብረማርቆስ፣ በደብረታቦር፣ ቆቦ እና ደብረታቦር ከተሞች የምርምርና ስልጠና ማዕከላትን በመክፈት ላይ የሚገኝና ተደራሽነቱን በማሳደግ ለተማሪዎች በሚያመች መልኩ ትምህርትና ሥልጠና እየሰጠ ነው፡፡ በተለያዩ የሀገር አቀፍና ክልላዊ የማህበራትና ጥምረት ላይ በንቃት በማሳተፍ የሃገሪቱንና የክልሉን ማህበረሰብ ተጠቃሚ የሚያደርጉ ማህበረሰብ ተኮር ሥራዎችን ይሠራል፡፡ በምርምር ዘርፍ ከጊዜ ወደ ጊዜ በትኩረትም ሆነ በበጀት እያደገ መምጣቱ በምርምር የተገኙ ውጤቶችን በተግባር በመፈተሽ ወደ ማህበረሰቡ የማሸጋገር ሥራዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደጉ መጥተዋል፡፡ ከ70 በላይ የሀገር ውስጥና የውጭ ተቋማት፣ ድርጅቶች፣ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት የአቅም ግንባታ፣ የምርምር፣ የማማከር ሰፊ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ በተያዘው አምስት አመትም ይህንን ቁጥር ለማሳደግ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተሰሩ ነው፡፡

በዩኒቨርሲቲው በአጠቃላይ እየተከናወኑ የሚገኙ ሥራዎችን በጠንካራ የውስጥና የውጭ ተግባቦት፣ በዕቅድ በመምራት የበለጠ የማስተዋወቅ፣ የማጉላት፣ ማህበረሰቡ እንዲገነዘብ የማድረግ ዓላማ ያነገበ ጽ/ቤት ተቋቁሞ ባለፉት 7 ዓመታት የመገናኛ ብዙኃን እና ሌሎች የተግባቦት ዜዴዎችን በመጠቀም የዩኒቨርሲቲውን ገጽታ ለመገንባት ዘርፈ ብዙ ተግባራት እየተካሄዱ ነው፡፡ ከብዙ በጥቂቱ ሐውልተ ጥበብን በመገንባት፣ ዩኒቨርሲቲው የራሱን መዝሙር በማዘጋጀት፣ ልዩ ልዩ የስጦታ ዕቃዎች ላይ የዩኒቨርሲቲውን ዓርማ በማተም የማስተዋወቅ ሥራ ተሰርቷል፡፡ ድረ-ገጽን በመጠቀም ከ2004 ዓ.ም፣ ማህበረሰብ ሚዲያን በመጠቀም ከ2006 ዓ.ም፣ ናይል ጋዜጣን በ2005 በማቋቋም (ከዚህ ዓመት በፊት ልዩ ልዩ ህትመቶች እንደነበሩ ይታወሳል)፣ በተያዘው ዓመት ከአማራ ብዙኃን መገናኛ ድርጅት ጋር በመተባበር ‹‹መስኮተ ጥበብ›› የተሰኘውን የቴሌቪዥን ሥርጭት ጀምሯል፡፡ በዩኒቨርሲቲው የሚከናወኑ ዘርፈ ብዙ የመማር ማስተማር፣ ምርምር፣ ማህበረሰብ አገልግሎትና የእውቀትና የቴክኖሎጅ ሽግግር ቱሩፋቶች ለማህበረሰብ የሚደረሱበትን ድልድይ ለመፍጠር ታስቦ ነው ‹‹መስኮተ- ጥበብ›› የተጀመረው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የዩኒቨርሲቲው ምሁራን በተፈጥሮም ሆነ በማህበረሰብ ሳይንሶች የሰሯቸው ሥራዎች ከመደርደሪያ ወርደው የማህበረሰቡን ችግሮች ለመፍታት እንዲውሉ ለማድረግ ዓይነተኛ መሣሪያ ነው፡፡

የቴሌቪዥን መርኃ ግብሩ የዩኒቨርሲቲውን ሁኔታ በሚገባ እንዲያሳይ የሁሉም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ተሳትፎ በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ የዩኒቨርሲቲው መላው ማህበረሰብ መረጃ በተጠየቁበት ጊዜ ቀና ትብብር በማድረግና የሚተላለፈውን መርኃ ግብር በመተቸት የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርግ ናይል ትጠይቃለች፡፡

**እውነትን መፈለግና ለሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!**

## ቁልፍ መልዕክት

# የገጠር ልማት በራዕይ ጥበብ 2017

ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት

ራዕይ ጥበብ 2017 በዕውቀት ላይ የተመሰረተ የገጠር ልማት እንዲመጣ ዩኒቨርሲቲው ቁልፍ ሚና እንዲጫወት አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡ ይህን አቅጣጫ መሰረት በማድረግ የራዕይ ጥበብ 2017 ጉዛችን ባለፉት አምስት አመታት በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በዚህ ጽሑፍ የገጠር ልማት ከራዕይ ጥበብ 2017 አንፃር እንዴት እንደተቀመጠና ከተግባራዊ ድርጊት አኳያም ገጽታው ምን እንደሚመስል በአጭሩ ይቀርባል፡፡ በዚህ መነሻ ሀሳብ መሠረት የዩኒቨርሲቲያችን ማህበረሰብ ተጨማሪ ሀሳቦችን በማንሳት ክርክር አድርጎበት ሀሳቡንና ተግባራዊ ገጽታውን በተሻለ መልኩ የምንገነዘብበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

የገጠር ልማት ስንል በገጠሩ የሚኖሩ ዜጎች የገቢ፣ የጤናና የትምህርት ሁኔታዎች መሻሻልን ያቀፈ ሀሳብ ነው፡፡ መገለጫዎቹም በእያንዳንዱ የገጠር ነዋሪ ገቢ፣ ጤናና የትምህርት ሁኔታ የሚታዩ ናቸው፡፡ ገቢን ዘርዝረን ስናየው በገንዘብ ሊተመን የሚችለውን የሰብል፣ የእንስሳትና ሌሎች የገቢ ምንጮችን የሚያቅፍ ነው፡፡ እንደሚታወቀው መሬት ውስን ነው፡፡ በመሆኑም የአንድ የገጠር ነዋሪ ገቢ መሬት በመጨመር ማሳደግ የሚል ስሌት ውስጥ አንገባም፡፡ በተግባር በግለሰብ ደረጃ የተያዘው መሬት ሊሰፋና ሊጠብ የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር ቢችልም በሀገር ደረጃ የማይጨመርና ሊሰፋ የማይችል ነው፡፡

የዩኒቨርሲቲያችን ተመራማሪዎችና ተማሪዎች እንዲመልሱት በራዕይ ጥበብ 2017 የተጠየቁት ጥያቄዎች የገጠር ነዋሪዎችን ገቢ በምን ምልኩ ማሳደግ ይቻላል? የሰብል ምርትና ምርታማነት ለመጨመር የሚጠቅመንና በኛ ነባራዊ ሁኔታ ልንተገብረው የምንችለው ዕውቀትና ቴክኖሎጂ የትኛው ነው? እንዴትስ ተምረን የኛ አድርገን በተግባር እናውለው? በሂደትስ ይህን ዕውቀትና ቴክኖሎጂ እንዴት እናዳብረው? የሚል ነው፡፡ እነዚህ ተመሳሳይ ጥያቄዎች የእንስሳት ምርትና ምርታማነት ከመጨመር አንፃርም ተቀምጠዋል፡፡ የገጠር ነዋሪዎች ከሰብልና እንስሳት ምርት ጋር ብቻ ተቆራኝተው ሊቀጥሉ አይችሉም፡፡ በመሆኑም የገቢ ማግኛ መንገዶች በተለምዶ ከነበሩት ምንጮች በተጨማሪ አዳዲስ ዘርፎች ሊፈጠሩ ይገባል፡፡ ከዚህም አኳያ እነዚህ ሊፈጠሩ የሚገባቸውን የገቢ ምንጮች እንዴት እንጀምራቸው? እንዴት እናስፋፋቸው? እንዴት በራሳችን እናበልጽጋቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ መንገዱን የማሳየት ስራ ልንሰራ እንደሚገባ ራዕይ ጥበብ 2017 ያስቀምጣል፡፡

አንድ ሰው ሆቴል ከፍቶ ሲሳካለት ሁሉም ሆቴል ለመክፈት መሯሯጥ፤ አንዱ ውጪ ሀገር ሂዶ ሲያልፍለት ሁሉም ወደ ውጪ መሯሯጥ፤ አንዱ የጀበና ቡና ሠርቶ ሲያልፍለት ሁሉም ወደ ጀበና ቡና የሚሯሯጠው በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ዕይታ ዩኒቨርሲቲያችንና መሰል ተቋማት ማሳየት ስላልቻልን በድንገተኛ ተሰርቶ ያዋጣንና የጥቂት ሰዎችን ምሳሌ ዜጎቻችን እንዲከተሉ አድርገናቸዋል፡፡ በድንገተኛ አጋጣሚ የተገኘን ስሌት መድገም ከባድ ነው፡፡ የዚህ አይነት ስሌት እንዴት እንደተገኘ መቀመርና ሌሎች እንዴት ሊደግሙት እንደሚችሉ ማስተማር ከባድ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ዜጎች የመጨረሻውን ውጤት ብቻ በማየትና በመማለል ይህን ስሌት ለማስመዝገብ የሚከተሉት መንገድ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ አይሆንም፡፡ በመሆኑም የመሳካቱን ጉዳይ ማወቅ አዳጋች ነው፡፡

በተለምዶ የገጠር ዜጎች ገቢ የሚያገኙባቸውን መንገዶች ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ እውቀትና ክህሎት ይጠይቃል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አዳዲስ የገቢ ማስገኛ መንገዶችን ለመፍጠር እውቀት ይጠይቃል፡፡ ይህን እውቀት ታጥቀን ገቢያቸው የሚያድግበትን ብልሀት መፍጠር ወሳኝ ነው፡፡ ዜጎች ለመምህራንና ሠራተኞች ደመወዛችንን እንዲሁም ለተማሪዎች የትምህርታቸውን ወጪ በመሸፈን የሚያስተምሩንና እንድንመራመር ገንዘብ የሚያፈሱልን፡፡ ስለሆነም ክፍል ውስጥ ስንማር፣ ስናነብ፣ ስንመራመር የምናገኘው እውቀት ፋይዳው የሚመዘነው እነዚህን ተጨባጭ ችግሮች በማገናዘብ ነው፡፡ በገባን ልክ እየተገበርን፣ የሚሰራውን እያጎለበትንና የማይሰራውን እየጣልን በተግባር ሜዳ የሚሰራ የገቢ ማሳደጊያ ብልሀት መፍጠር እንችላለን፡፡ ራዕይ ጥበብ 2017 የገጠር ልማት ገቢን በአጭሩ ከላይ በገለጽነው አግባብ ያየዋል፡፡ ከትምህርትንና ጤና አንፃር በሌላ ጽሁፍ እናቀርባለን፡፡

**ራእይ ጥበብ 2017ን እናሳካለን!**

# አበይት ዜናዎች...

## ሂሳብን አዝናኝና ተግባር ተኮር በማድረግ ማስተማር እንደሚቻል ተጠቆመ

በአበባ ሀብቱ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማሕበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ከሂሳቢ ት/ክፍል ጋር በመተባበር በ"math Camp" ፕሮግራም ለ3ኛ ጊዜ ስልጠና ሰጠ፡፡ የስልጠናው ዋና አላማ ሂሳብን አዝናኝና ተግባር ተኮር በሆነ መንገድ የሚሰጥበትን መንገድ በማሳየት ትምህርቱን በሕብረተሰቡ ዘንድ ተወዳጅ ማድረግ ነው፡፡

የምርምርና ማሕበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው የተማሪዎች የሂሳብ እውቀት ብቃት ለማጐልበት ዩኒቨርሲቲው በቁርጠኝነት እየሰራ እንደሚገኝ ገልጸው ሆኖም ግን በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎችም ካልተሰጠ ‹የጋን መብራት› እንደሆነ በመጥቀስ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የመጡ ተሳታፊዎች የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲን ተሞክሮ በመውሰድ በአካባቢያቸው ለሚገኙ ተማሪዎች እንዲያዳርሱ አደራ ብለዋል፡፡

የእንኳን ደህና መጣችሁና ለስልጠናው አዘጋጆችና መምህራን እንዲሁም ተማሪዎች የምስጋና መልዕክታቸውን ያስተላለፉት የሂሳብ ት/ክፍል ኃላፊ ዶ/ር ጉርጁ አውግቸው የሳይንስና ቴክኖሎጂ መጐልበት ለአንድ ሀገር እድገት ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ጠቁመው ከእያንዳንዱ ፈጠራና ምርምር ጀርባም ተጠቃሚው የማያውቃቸው እንደ ዋና

ወደ ገጽ 15 ዞሯል

## ዩኒቨርሲቲዎችን ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ጋር በማስተሳሰር የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማጠናከር እንደሚያስፈልግ ተገለፀ

በአበባ ሐብቱ

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በምርምር የተገኙ ግኝቶችን አጠናክሮ ለመቀጠልና አዳዲስ የቴክኖሎጂ ማሻሻያዎችንና እውቀቶችና በተደራጀና ቀጣይነት ባለው መልኩ ወደ ኢንዱስትሪዎች ለማስተላለፍ ከኢንዱስትሪዎችና አጋር ድርጅቶች ጋር የውይይት መድረክ በቴክኖሎጂ ተቋም አካሄደ፡፡

የቴክኖሎጂ ተቋሙ ማኔጂንግ ዳይሬክተር ዶ/ር ሲሳይ ገረመው የውይይቱን አላማ ሲገልጹ ዩኒቨርሲቲውን ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ጋር በማስተሳሰር የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማጠናከር የጋራ መድረክ መፍጠር፣ የትምህርት ጥራት ለማሳደግና ተግባር ተኮር ትምህርትን ለማሻሻል የኢንዱስትሪዎችን ሚና መለየትና ቀጣይነት እንዲኖረው ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ ማድረግ ነው፡፡

የተቋሙ ተመራቂ ተማሪዎች በየትምህርት ክፍላቸው የተለያዩ የፈጠራ ስራዎቻቸውን አቅርበው በውይይቱ ተሳታፊዎች ተጎብኝተዋል፡፡ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በርካታ የሀገር ኩራት የሆኑ አመርቂ ስራዎችን እያከናወነ መሆኑን በጉብኝታቸው ወቅት መገንዘባቸውን ተናግረዋል፡፡ እነዚህን ስራዎቻቸውን የበለጠ ለማሳደግ ከኢንዱስትሪዎች ጋራ መስራት እንዳለባቸውና ከዚህ የበለጠ ውጤታማ መሆን እንደሚችሉ አስምረውበታል፡፡ ከተለያዩ የግልና የመንግስት ኢንዱስትሪዎች፣ ሴክተር መስሪያ ቤቶችና የዩኒቨርሲቲ ምሁራን እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላት በውይይቱ ተሳትፈዋል፡፡

## ኮሌጁ የስርዓተ ትምህርት ግምገማ አካሄደ

በትዕግስት ዳዊት

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ የ3ኛ ዲግሪ (PhD in Soil Science) እና የ2ኛ ዲግሪ (MSC in integrated water shed management) ስርዓተ ትምህርትን የሚገመግም አውደ ጥናት አካሄደ፡፡

የኮሌጁ ዲን ዶ/ር በላይነህ አየለ ኮሌጁ እያከናወናቸው ያሉትን ተግባራት ገልጸው ግብርና የሀገራችን የጀርባ አጥንት እየሆነ በመምጣቱ እነዚህን ሁለት የስርዓተ ትምህርቶች ማዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ስርዓተ ትምህርቱን ለመገምገም ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ለመጡት ምሁራን ምስጋና አቅርበዋል፡፡

የ3ኛ ዲግሪ ስርዓተ ትምህርቱን ያቀረቡት ዶ/ር እንየው አድጎ ሲሆኑ ፕሮፌሰር ፋሲል ከበደ እና ዶ/ር ሽለመ በየነ ያላቸውን ገንቢ አስተያየትና መሻሻል አለባቸው ያሏቸውን ጉዳዮች አቅርበዋል፡፡ በተጨማሪም ትምህርቱ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይወሰን ከተለያዩ የአለም ሀገራት ተማሪዎችን ተቀብሎ የሚያስተምርበትን ሁኔታ ኮሌጁ እንዲያመቻች አሳስበዋል፡፡

በእለቱ በዶ/ር ደረጀ ፀጋዬ የቀረበው ሌላው የስርዓተ ትምህርት ግምገማ 'MSC Degree in Watershed Management' ሲሆን በዶ/ር ፈንታው ይመር እና በአቶ አሰፋ ደረበ የስርአተ ትምህርቱ ሂደት እና ይዘት ላይ ማብራሪያ ተሰጥቶበታል፡፡ በአውደ ጥናቱ ላይ የተሰጡትን አስተያየቶች በመቀበል ስርአተ ትምህርቶቹ በቅርቡ ተቀርጸው እንደሚቀርብ ታውቋል፡፡

## የፓሊዬቲቭ ሆስፔስ ኬር አገልግሎት በስፋት መሰራት ያለበት የህክምና ዘርፍ መሆኑ ተገለፀ

በየማነ ገብሩ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከሰዎች ለሰዎች ግብረ ሰናይ ድርጅት ጋር በመተባበር ሕመማቸው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ ሕመምተኞችና ቤተሰባቸው ከጽኑ ሕመም ጋር ተያይዞ የሚያጋጥማቸውን ችግር በመከላከል፣ ስቃያቸውን በመቀነስና በመቆጣጠር ስነ ልቦናዊ፣ ማሕበራዊና መንፈሳዊ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል የሕክምና ዘርፍ ለመጀመር የአንድ ቀን አውደ ጥናት አካሄደ፡፡

የአውደ ጥናቱ ዋና ዓላማ የፅኑ ሕሙማን ሁለንተናዊ እንክብካቤ (የፓሊዬቲቭ ሆስፔስ ኬር) በኢትዮጵያ በስፋት ራሱን ችሎ እንደሌሎች የሕክምና ዘርፍ መሰጠት የሚያስችል ልምድ መቅሰምና ራሱን የቻለ መመሪያ እንዲቀረፅ ማድረግ ነው፡፡

የጽኑ ህሙማን ሁለንተናዊ መድህናዊ ክብካቤ በኢትዮጵያ ብሎም በአፍሪካ ብዙ ያልተሰራበት የሕክምና ዘርፍ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን በአውደ ጥናቱ ላይ በቀረቡ ፅሁፎች የኢትዮጵያ ማህበራዊ ግንኙነት (ማህበራዊ ሕይወት) ለዘርፉ መስፋፋትና አገልግሎት ለመስጠት የተመቸ ማህበራዊ እሴት እንደሆነ ተነግሯል፡፡

አውደ ጥናቱን በንግግር የከፈቱት የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ማተቤ ታፈረ ዩኒቨርሲቲው በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የጤና ችግር ለመፍታት በተለያዩ የሕክምና ሙያ ባለሙያዎችን ከማሰልጠን በተጨማሪ ለመማር ማስተማር የሚያገለግል ሆስፒታል በማስገንባት ላይ መሆኑን ገልፀው ይህንን አዲስ የሕክምና ዘርፍ ለማስፋፋት ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሰራ ተናግረዋል፡፡ በአውደ ጥናቱም ከአሜሪካ፣ ከሆስፒስ ኢትዮጵያና ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የመጡት ባለሙያዎች ጥናታዊ ፅሁፋቸውን አቅርበው ሰፊ ውይይት ተካሂዷል፡፡

## ዩኒቨርሲቲው ከሀምቡርግ ዩኒቨርሲቲ ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ

በሙሉጉጃም አንዱአለም

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከሀምቡርግ ዩኒቨርሲቲ ጋር በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባሕል ጥናት ዙሪያ በጋራ ለመስራት ተፈራረሙ፡፡ ስምምነቱ ሁለቱ ተቋማት በጋራ በመተጋገዝ ስለ ኢትዮጵያ ቋንቋዎች ግዕዝን ጨምሮ በጋራ ለመወያየትና የጋራ የሆኑ የጥናት መስኮችን ለማካሄድ የሚቻልበትን መንገድ ለማመቻቸት እንዲሁም የአካባቢውን ማሕበረሰብ የአኗኗር ዘዴ ወደ ዘመናዊ መቀየር የሚቻልበት ሰፊ ጥናት ለማካሄድ ያስችላል፡፡

የስምምነቱ ዋና ዓላማ ከዩኒቨርሲቲው አባይ የባህልና ልማት ጥናትና ምርምር ማዕከል ጋር በጋራ ለመስራትና «የኢትዮጵያ ሴማዊ ቋንቋዎችና ባሕል ጥናት» በተሰኘ የትምህርት መስክ የድህረ- ምረቃ መርኃ ግብር ለመክፈት መሆኑን ጀርመን አገር ከሚገኘው ሒዮብ ሉዶልፍ (HLLES) የኢትዮጵያ ጥናት ማዕከል የመጡት ዶ/ር ጌቴ ገላዬ እና ዶ/ር ዴቪስ ኖርዩትሲን ገልፀዋል፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው ለእንግዶች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ካስተላለፉ

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

## 7ኛው አመታዊ የምስራቅ አፍሪካ መሬት አስተዳደር ጉባኤ ተካሄደ

በአምሳሉ ጥላሁን

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ መሬት አስተዳደር ተቋም 7ኛውን ዓመታዊ የምስራቅ አፍሪካ የመሬት አስተዳደር ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጥምረት ጉባኤ ለሁለት ቀናት አካሄደ፡፡

በጉባዓው ላይ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ያደረጉት የመሬት አስተዳደር ተቋም ዳይሬክተር ዶ/ር አቻምየለህ ጋሹ የጉባኤው መካሄድ ዋና ዓላማ ተቋማቱ በመሬት አስተዳድርና አያያዝ ላይ የእውቀት፣ የክህሎትና የልምድ ልውውጥ ለማድረግ እንዲሁም በምርምር፣ በማህበረሰብ አገልግሎትና በስልጠናዎች ላይ አብሮ ለመስራት እና የተቋማቱን ግንኙነት ከፍ ለማድረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ዘመናዊ የሆነ የመሬት አስተዳድር ስርዓት በመዘርጋት ዜጎችን ከመሬት ሁሉን አቀፍ ተጠቃሚ ለማድረግ እና በመሬት ምክንያት የሚከሰቱ ግጭቶችን ለማስወገድ የሰለጠነ የሰው ሃይል እንደሚያስፈልግ

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

## የተማሪዎች ፈጠራ ሥራ ተጐበኘ

በትዕግስት ዳዊት

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት በባሕር ዳር ከተማ ድልችቦ ት/ቤት ውስጥ ያስገነባው የሳይንስ ማበልፀጊያ ቤተ ሙከራ ማዕከል በ2007 ዓ.ም በተማሪዎች የተሰሩት የፈጠራ ስራዎች ጥሪ ለተደረገላቸው አካላትና የተማሪ ቤተሰቦች እንዲሁም ለዩኒቨርሲቲው ማሕበረሰብ አስጐበኘ፡፡

ተማሪዎቹ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፅንሰ

ወደ ገጽ 15 ዞሯል

# አበይት ዜናዎች…

## ዜና ትንታኔ

### ለ2017 ራዕይ ስኬት ሁሉም የዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ መረባረብ እንዳለበት ተገለፀ

በአምሳሉ ጥላሁን

ባሕርዳር ዩኒቨርስቲ በ2017 ዓ.ም አፍሪካ ውስጥ ካሉ 10 ምርጥ የምርምር ዩኒቨርስቲዎች አንዱ ለመሆን ራዕይ ሰንቆ እየሰራ ይገኛል፡፡ ይህ ራዕይ የሚሳካው አመራሩና መምህራን እንዲሁም የአስተዳድር ሰራተኞች በጋራ ሲረባረቡና ለጋራ አላማ ሲቆሙ ነው፡፡ በመሆኑም ሁሉም የዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ በጋራ በመሆን መንቀሳቀስ ለራዕዩ ስኬት የጎላ አስተዋጽኦ አለው፡፡

ዩኒቨርሲቲው ለራዕዩ ስኬት ዘጠኝ የተለያዩ የምርምር አቅጣጫዎችን በመምረጥ ከውሃ፣ ከባዩ ቴክኖሎጂ፣ ከትምህርት፣ ከሀይል አጠቃቀም፣ ከጨርቃጨርቅና ፋሽን ዲዛይን፣ ከጅኦስፓሻል ቴክኖሎጅ፣ ከዲሞግራፊክ ሰርቪላንስ፣ ከባህልና እድገት እንዲሁም ከኢኮኖሚክስ ጋር ተያያዥንት ያላቸው ማዕከላትን በማቋቋም እየሰራ ይገኛል፡፡ በመማር ማስተማሩ ዘርፍም ቢሆን ከመደበኛው ማስተማር ዘዴ በተጨማሪ በማታው፣ በክረምት፣በርቀት መርኃ ግብር ለማህበረሰቡ እያዳረሰ ይገኛል፡፡ከዚህ በተጨማሪ ለሁለተኛና ሶስተኛ ዲሪግ ትኩረት በመስጠት እየሰራ ነው፡፡ በማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፍ ላይ ብዙ ስራዎች እየሰራ የአካባቢውን ማህበረሰብ እየጠቀመ ይገኛል፡፡ በዚህም ረገድ የመጀመሪያውን የአምስት ዓመት ዕቅድ (የራዕይ ጥበብ 2017ን የመጀመሪያ ምዕራፍ) በድል እንደተወጣነው ያመላክታል፡፡ ስለዚህ የሁለተኛውን የአምስት ዓመት ዕቅድ በድል ለመወጣት ከአመራሩ ጀምሮ እስከታች ያለው ሰራተኛ ድረስ መስተጋብር በመፍጠር መንቀሳቀስ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ የመጀመሪያውን የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ አጠናቀን የሁለተኛውን የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ለመጀመር በእንቅስቃሴ ላይ የምንገኝበት ወቅት ነው፡፡

ለዚህ እንቅስቃሴ ያመች ዘንድ የኢንፎርሜሽንና ስትራቴጅክ ኮሙኒኬሽን ም/ፕ/ጽ/ቤት በ2007 በጀት ዓመት ዩኒቨርስቲው መልካም የስራ አፈጻፀም ማካሄዱን ምክንያት በማድረግ በጥበብ ህንጻ ላይ ባዘጋጀው የእራት ግብዣ ላይ የተገኙት የዩኒቨርስቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ እንደተናገሩት በ2007 ዓ.ም ዩኒቨርስቲው መልካም የስራ አፈጻፀም ማካሄዱን በመግለጽ ለዚህ ስኬት መብቃት የሁሉም የዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ አስተዋጾያ በመሆኑ ምስጋና አቅርበዋል፡ ፡ ለ2017 ራዕይ ስኬትም ሁሉም የዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ ሊረባረብ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

ዓመቱን በሙሉ በስራ ተጠምዶ ለቆየ ሰራተኛ ዩኒቨርስቲው ምስጋና ማቅረቡ ለወደፊቱ ዕቅድ ስኬት ሐላፊነት (አደራ) መስጠት መሆኑ የሚያሻማ ጉዳይ አይደለም፡፡ በመሆኑም ሁሉም የዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ የተሰጠውን አደራ ለመወጣት ላይና ታች የማይልበት ምንም ምክንያት የለውም፡፡ ስለሆነም ሁሉም አካል ወደ ስራ ከመግባቱ በፊት ስለ ራዕይ ጥበብ 2017 እንዲሁም ስለ ዩኒቨርስቲው ተልዕኮው ማወቅ የመጀመሪያው ተግባር መሆን አለበት፡፡ ከዚህ በኋላ ነው ወደ ስራ አፈጻጸም መግባት ያለበት፡፡

### የዩኒቨርሲቲው ልሳናት ሚዛናዊና ገንቢ ትችት ማስተናገድ እንዳለባቸው ተገለፀ

በየማነ ገብሩ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲን ገፅታ ለመገንባት እየሰሩ ያሉት የሕትመትና የምስል የሚዲያ ተግባራት በራዕይ እና ተልዕኮ የተሻለ ግንዛቤ ከመፍጠራቸው በተጨማሪ የብዙሃን ሐሳብ ማንሸራሸሪያ፣ የአዳዲስ ሐሳቦችንና ዕይታዎች መፍለቂያ መሆን እንዳለባቸው ተገለፀ፡፡ ይህ የተገለጸው ናይል ጋዜጣ የተመሰረተችበትን ሁለተኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ የጋዜጣዋን ተነባቢነትና ተደራሽነት ለማስፋት ከባለ ድርሻ አካላት ጋር ውይይት በተደረገበት ወቅት ነው፡፡

ለውይይቱ መነሻ ሀሳብ በዩኒቨርሲቲው የጋዜጠኝነትና ስነ-ተግባቦት መምህር ዶ/ር ጀማል ሙሀመድ “የህትመት ሚዲያ ሚና” በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ፅሁፍ እንዲሁም የጋዜጣዋ የአንባቢያን የዳሰሳ ጥናት በዋና አዘጋጇ ወ/ሮ ፀጋነሽ ሙሉጌታ በኩል ቀርበው ሰፊ ውይይት የተደረገባቸው ሲሆን የናይል ጋዜጣን የአንባቢያን ቁጥር ለመጨመር ማሕበራዊ ኃላፊነት ያለበት ሚዛናዊና ገንቢ ትችት ማካተት፣ የዩኒቨርሲቲውን ራዕይና አቅጣጫ መሰረት በማድረግ ለሁሉም ግቢዎችና የስራ ክፍሎች በፍትሀዊነት ዕድል መስጠት፣ ለዘላቂ ተነባቢነት ቋሚ አምድ መፍጠር እና ሌሎች መሰረታዊ ሃሳቦች ተነስተዋል፡ ፡

በውይይቱ ላይ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ በተነሱ ነጥቦች ላይ ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግ ጠቁመው የተቋሙ ልሳናት በሚቀጥለው አምስት ዓመታት ከተቋሙ በተጨማሪ በባሕር ዳር ከተማ ብሎም በክልሉ ያሉትን ማሕበራዊ እሴቶችን በመዳሰስ አስተማሪና አዝናኝ በሆነ መልክ በመቀመር በስፋት መስራት እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡

በምክክር መድረኩ ላይ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት፣ ም/ፕሬዝዳንቶች፤ የጋዜጠኝነትና ስነ-ተግባቦት ትምህርት ክፍል መምህራን፣ የጋዜጣዋ አንባቢያንና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች የተሳተፉ ሲሆን የጋዜጣዋን ጥራትና በየጊዜው እያደረገች ያለችውን መሻሻል በማድነቅ የጋዜጣዋን ተነባቢነትና ተደራሽነት ለማሳደግ ገንቢ ሀሳብ ሰጥተዋል፡፡

ናይል በኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሙዩኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት አማካኝነት በወር አንድ ጊዜ ታትማ የምትሰራጭና ለማህበረሰቡ ስለዩኒቨርሲቲው መረጃ በማድረስ ተነባቢነትን እያገኘች ሁለት ዓመት የዘለቀች ጋዜጣ መሆኗ ይታወቃል፡፡

### ዩኒቨርሲቲው የንባብ ማዕከል ለመገንባት የመሰረት ድንጋይ አስቀመጠ

በሙሉጐጃም አንዱአለም

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማሕበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ከሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ ጋር በመተባበር በደብረ ታቦር ከተማ “አቦጊዳ የንባብ ማዕከል” የተሰኘ የንባብ ማዕከል ለመገንባት የመሰረት ድንጋይ አስቀመጠ፡፡

የዩኒቨርሲቲው የአማርኛ ቋንቋ ማበልፀጊያ ተቋም ዳይሬክተርና የፕሮጀክቱ አስተባባሪ ዶ/ር ሂሩት ካሳው የፕሮጀክቱን ዋና ዓላማ አስመልክቶ እንደተናገሩት ማዕከሉ የአካባቢውን ወጣቶች፣ ተማሪዎች፣ አዛውንቶች በንባብ ለማልማት የሚያስችሉ የተለያዩ መርኃ ግብሮችን ማለትም እንደ ስነፅሁፍ ምሽት፣ የንባብ ቀን፣ የቅኔና የስነቃል፣ የመሪዎች ወግ፣ የአዛውንቶች ወግ እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮችን ሣምንታዊ፣ ወርሃዊና ዓመታዊ ፕሮግራሞች የሚከናወኑበት ምቹና አረንጓዴ ማዕከል መገንባት ነው፡ ፡ ዶ/ር ሂሩት አክለውም ማዕከሉ ለዩኒቨርሲቲው የአማርኛ ቋንቋ ተመራማሪዎችና መምህራን የተለያዩ ችግር ፈች ምርምሮች የሚያካሂዱበት እንደሚሆን ተናግረዋል፡፡

በዕለቱ የደብረታቦር ከተማ አስተዳደር ም/ከንቲባና የትምህርት ጽ/ቤት ሃላፊ አቶ ደሳለኝ አበበ፣ የከተማው ኢንዱስትሪና ከተማ አገልግሎት ሥራ አስኪያጅ አቶ አዳነ ጌታነህ በጋራ የማዕከሉን መገንቢያ የቦታ ካርታ ለባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ተወካይ አቶ አድማሱ ፈንታ፣ ለዶ/ር ሂሩት ካሳው እና ለሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ ዲን ዶ/ር ስዩም ተሾመ አስረክበዋል፡፡

አቶ ደሳለኝ ዩኒቨርሲቲው እያበረከተ ላለው ዘርፈ ብዙ የማሕበረሰብ አገልግሎት በተለይ በአማርኛ ቋንቋ ማበልፀግ ዙሪያ መልካም ተሞክሮዎችን እያበረከተ መሆኑን ገልፀው የከተማው አስተዳደር የቦታ ጥያቄውን ተቀብሎ በአጭር ጊዜ ውስጥ ምላሽ እንዲሰጥ ያደረገው የፕሮጀክቱ ራዕይ ለአካባቢው ማሕበረሰብ ያለው ፋይዳ የላቀ በመሆኑ 15,000 ካ.ሜ ስፋት ያለው ቦታ መስጠቱን ገልፀዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ተወካይ አቶ አድማሱ ዩኒቨርሲቲው በምርምርና ማሕበረሰብ አገልግሎት ዙሪያ ከፍተኛ ለውጥ እያስመዘገበ እንደሆነና ከምርምር እስከ ስርፀት ያለው የአሰራር ስርዓት ይበል የሚያሰኝ መሆኑን ገልፀው ይህን በጐ ሥራ ለማጐልበት በደቡብ ጐንደር ዞን የንባብ ፓርክ መመስረቱ አኩሪ ተግባር ስለሆነ ለከተማ አስተዳደሩ ምስጋና አቅርበዋል፡፡

ዶ/ር ስዩም በበኩላቸው የንባብ ማዕከሉን እውን ለማድረግ የተቀመጠው የመሰረት ድንጋይ በአጭር ጊዜ ግንባታው የሚከናወንበት መንገድ እንደመቻችና የታለመለትን ግብ እንዲመታ ሁሉም የበኩሉን ድርሻ መወጣት እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡

### ዩኒቨርሲቲው ከሀምቡርግ …

ከገጽ 4 የዞረ

በኋላ የዩኒቨርሲቲዎቹ በጋራ መስራት ፋይዳው የጐላ በመሆኑ ሁለቱም ተቋማት የበኩላቸውን ድርሻ ወስደው ስምምነቱን ወደ ተግባር መለወጥ እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡ ዶ/ር ተስፋዬ አክለውም ሁለቱም ዩኒቨርሲቲዎች በቂ መምህራን ከመመደብ ጀምሮ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን በመመካከርና የጋራ ግንዛቤ በመፍጠር መፍታት እንዲቻልና ከታቀዱት ሁለት ግቦች ባሻገር ሌሎች ተግባራትን በማካተት መስራት እንደሚያስፈልግ ገልፀዋል፡፡

ስምምነቱ ላይ የአባይ የባህልና ልማት ጥናትና ምርምር ማዕከል ዳይሬክተር፣ የሂዩማኒቲስና የሶሻል ሳይንስ ፋኩልቲ ዲኖች፣ የድህረ ምረቃ ምክትል ዲን የተሳተፉ ሲሆን ሊሰራ የታሰበው ሥራ አስፈላጊና ጠቃሚ በመሆኑ ሀሳቡን ይዘው ለመጡት እንግዶች ምስጋና አቅርበው የሁለቱ ዩኒቨርሲቲዎች የጋራ ስራ ዘላቂ እንዲሆንና እንዲጠናከር እንዲሁም የታሰበው የድህረ-ምረቃ ትምህርት ወደ ሶስተኛ ዲግሪ እንዲያድግ ርብርብ ማድረግ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

# የዩኒቨርሲቲው ተማሪ ማስታወሻ

(ከሚያዚያ ወር ዕትም የቀጠለ)

በፈታሒ በቃሉ

የፖሊስ አዛዡ በተገኘው ፍንጭ መሠረት ምርመራውን ለማጠናከር ማቀዱን ስለተረዳሁ መልካሙን ነገር እየተመኘሁ ከጠባቂ ፖሊሱ ዘንድ ተቀምጬ እያጠናሁ እያለ፣...... ፖሊሱ ወደ እኔ በመጠጋት ‹‹አንተ እድለኛ ነህ:: በቀላሉ የምትገላገል ይመስለኛል:: ለእኔ ግን ብዙ ጠቅመኸኝ ነበር:: ካለ በኋላ ‹‹ኢንስፔክተርም ቢሆን የምርመራውን ትኩረት ከአንተ ላይ ሣያነሣ አይቀርም::›› አለኝ እኔም ‹‹ታዲያ ሁኔታው እንደዚህ ከሆነ ለምን አትፈቱኝም?›› አልኩት:: ፖሊሱም ትንሽ ፈገግ አለና ‹‹ቆይ እስኪ አትቸኩል ምን አልባት ዋስ ትጠራና ሰሞኑን ትወጣ ይሆናል›› በማለት ትንሽ ተስፋ ሰጠኝ:: እንደዚያ ሲለኝ ልቦናዬ ለመፈታት ስለጓጓ ማንበብ አልቻልሁም:: በዚህም ምክንያት ማጥናቱን ፍፁም ተውኩት:: ወዲያው ደግሞ ዋስስ ቢሆን ከየት አገኛለሁ? በማለት ሌላ ሀሳብ መጣብኝ::

በዕለቱ በግምት ከሁለት ሰዓት በኋላ መታወቂያዎችን እንዲሸጥ ያስረከበው ወጣት ጎረምሣ ተይዞ መጣና ሲጠየቅ በፍፁም እኔ አልሰጠሁትም በማለት ካደ:: ወዲያው ተቀበልኩት ያለው እሥረኛ ተጠርቶ ሁኔታውን እንዲያስረዳ መርማሪው በመጠየቁ በትክክል እሱ እንደሰጠው ሲቀበለውም ያዩ እንደነበሩና ከሸጠበት ገንዘብም የእሱን ድርሻ አንድ መቶ ብር እንደሆነ አስረዳ:: መርማሪ ፖሊስም ሲጽፍ ቆየና ቀና በማለት ‹‹እንግዲህ ማስረጃዎች እየቀረቡብህ ነው::›› ሲለው ‹‹አይ! በቃ ሰጥቼዋለሁ›› አለ:: መርማሪው እየጻፈ እያለ ካርዶችን ሰጥተኸኛል ያለውን እሥረኛ ከንፈሩን በመንከስ ዐይኑን ሲያፈጥበት ‹‹ኧረ! እያንገራገረኝ ነው::›› በማለቱ መርማሪው በግልፍተኝነት አንዴ በጥፊ አቀመሰውና እዚህም ገብተህ ደግሞ አትተውም በማለት ሊደግመው ሲል እጆቹን በፊቱ ላይ በማድረግና ዐይኑን በመጨፈን አንገቱን ደፋና ‹‹አሁን ምን አደረግሁ›› ይል ጀመር:: በመቀጠል እኔን እንዴት እንደሰረቀኝ እንዲያስረዳ ሲጠየቅ ወደ እኔ እየተመለከተ ‹‹የት ላይ ነበር የወሰድንብህ? እስቲ አስታውሰኝ›› በማለት ጠየቀኝ:: እኔም በጣም በመገረም ‹‹ወደ አባይ ማዶ በሚወስደው ታክሲ...›› ብዬ የጀመርኩትን ዐረፍተ ነገር ሳልጨርስ...... መርማሪው ፖሊስ ጣልቃ በመግባት ‹‹አታለባብሰው በደንብ ተናገር›› በማለት ተቆጣ:: ‹‹አዎ በር ላይ ነው አይደል›› አለና አሁንም ወደ እኔ ሲመለከት ግንባሬን ቀና በማድረግ አዎ በማለት ስመልስ፣ ፖሊሱ የበለጠ ቆጣ ብሎ በድጋሜ ‹‹እንዴት እንደወሰድኸው ራስህን ችለህ አስረዳ›› አለ:: እሱም እንደማይለቀው ሲገነዘብ አዎ ወደ ታክሲው ሊገባ ሲል ሁለት ሆነን በግራና በቀኝ አጣብቀን ከያዝነው በኋላ ከስፖርት ቱታው ጃኬት ኪስ ቦርሣውን አወጣሁና ወሰድሁት አለና ዝም ሲል፣ መርማሪው ቀጠለና ‹‹ብሩንስ የት አደረሣችሁት?›› በማለት ጠየቀው:: ሌባውም ምን ጥያቄ አለው? ያው አገልግሎት ላይ ውሏል፣ ሲለው አቋረጠና ‹‹ለመሆኑ አሁን ምን ያህል ገንዘብ ይዘሃል?›› በማለት ጠየቀው፣ ሌባውም፣ ግንባሩን እያሻሼ አሁን የያዝሁት የእሱን ብር ሣይሆን የራሴን ነው አለ:: መርማሪው ይህን ሲሰማ ‹‹የተጠየቅኸው ምን ያህል አለህ? ነው እንጅ የብሩን ምንጭ አይደለም:: ስለዚህ አሁን መጠኑን ብቻ ተናገር›› ሲለው ሲያስብ ቆየና ምን ያህል እንደሆነ ልቁጠረው አለና፣ ከየኪሶቹ ብዙ የተጨመዳደዱ የመቶ፣ የአምሣ፣ የአስር፣ እንደዚሁም ጥቂት የአምስት እና የአንድ ብር ኖቶች እያወጣ በጠረጴዛው ላይ በመዘርገፍለቆጠራ በሚያመች መልኩ ከአደራጀ በኋላ ሲቆጠረው አንድ ሺ ሰባት መቶ አምሣ ስምንት ብር ሆነ:: ከዚያም ሲመለከተው ቆዩና እሽ! አሁን ከልጁ የወሰድኸውን አትመልስለትም በማለት ጠየቀው:: ሌባውም ስንት እንደሆነ ይናገርና በአንተ ፊት ይውሰድ:: ብቻ ነገሩን ቀለል አድርገህ ብትለቀኝ ጥሩ ነው በማለት ይማፀነው ጀመር:: እኔም የወሰደብኝን ገንዘብ መጠን ስናገር ቆጥሮ ሊሰጠኝ ሲል፣ ቆይ እሱ ችግር የለም ይደርሣል:: አለና በመቀጠል ቅድም ስትናገር ለሁለት አጣብቃችሁ በመያዝ እንደሰረቃችሁት ነግረኸኛል:: ታዲያ ከአንተ ጋር ተባብሮ አጣብቆ በመያዝ የረዳህ ስሙ ማን ነበር? በማለት ሲጠይቀው ስሙን ነገረው:: መርማሪው ጥሩ! ስለዚህ ጓደኛህን እንዴት እንደምናገኘው ንገረኝ ሲለው፤ ሌባውም ምን ችግር አለ:: ከ......... ፑል ሃውስ ስለማይጠፋ በቀላሉ እዚያ ታገኙታላችሁ አለና ስሙን ከነአባቱ እንደዚሁም የሞባይል ስልኩን ጨምሮ ተናገረ::

> ከውጭ አንድ ፖሊስ ጠራና
> ሌባው ሲቆጥረው የነበረውን ብር
> እያመለከተ ይህንን ገንዘብ በኤግዚቢትነት
> መዝግባችሁ አስቀምጡት በማለት ትዕዛዝ ከሰጠ
> በኋላ፤ ሌባውን ወደ ሌላ ፖሊስ ጣቢያ
> እንዲወስዱት ትዕዛዝ ሰጠ::

በመቀጠልም ከውጭ አንድ ፖሊስ ጠራና ሌባው ሲቆጥረው የነበረውን ብር እያመለከተ ይህንን ገንዘብ በኤግዚቢትነት መዝግባችሁ አስቀምጡት በማለት ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ፤ ሌባውን ወደ ሌላ ፖሊስ ጣቢያ እንዲወስዱት ትዕዛዝ ሰጠ:: ከዚያም ወደ እኔ ዞር ብሎ በወንጀሉ አብረህ እንዳልተባበርህ በፍርድ ቤት ከተረጋገጠና ገንዘቡም በትክክል ያንተ መሆኑ ሲታወቅ ይሰጥሃል:: አለኝ:: በእርግጥ በውስጤ ገንዘቡ ሊጠቅመኝ እንደሚችል ቢገባኝም፤ ገንዘቡ ቀርቶብኝ ከዚህ እሥር ቤት የምላቀቅበት ጊዜ ናፈቀኝ:: ከዚያም ለምን አልነግረውም አልሁና እኔ እንኳን ገንዘቡ ቀርቶብኝ ብትፈቱኝ በማለት ኃሳብ ሳቀርብ መርማሪው ፖሊስ ቀና አለና አሁንስ አንተ በድርጊቱ ውስጥ አብረህ አለመኖርህ በምን ተረጋገጠ በማለት እንደገና ሲያስደነግጠኝ ፀጥ ብዬ ተመለስሁና መቆዘም ጀመርሁ::

በበነጋው ጠዋት መታወቂያዬን ገዛ የተባለው ሰው እንዳልተገኜ ጠባቂው ፖሊስ ነገረኝ:: በዚህም የተነሣ የመፈታት ዕድሌ እየመነመነ ሄደብኝ::

አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ አንድ ተጠርጣሪ ወንጀለኛ ምንጩ ያልታወቀ ዕቃ ሲሸጥ በመገኘቱ እጅ ተፈንጅ ተይዞ ገባ:: ሲሸጥ የተገኘው ተጠርጣሪ ከየት አምጥቶ ሲሸጥ እንደነበር ሲጠየቅ ከሆነ አልፎ ሃጅ ሰው ገዛሁት ቢልም ሲሻጣቸው የተገኙት ዕቃዎች ደግሞ ሰሞኑን ተዘረፈ የተባለው ሱፐር ማርኬት ባለቤት በብቸኝነት የሚሸጣቸው ዕቃዎች ስለሆኑ መርማሪው ፖሊስ ተጠርጣሪውን በአንክሮ እየተመለከተ ምርመራውን ቀጠለ::

እንደተለመደው በቅድመ ምርመራ የሚሙሉትን ዝርዝሮች ከሞላ በኋላ እሱነቱን የሚገልፅ መታወቂያውን ሲጠይቀው ጠፍቶኛል አለው:: ይህ በዚህ እንዳለ መታወቂያ የሸጠው እሥረኛ ይህንን ተጥርጣሪ ሲያዬው እሱ መሆኑን ለጠባቂው ፖሊስ ሲነግረው ወዲያው ይህ ወሬ ለመርማሪው ፖሊስ ሲደርሰው:: ለምን ትክዳለህ ለመሆኑ ፎርጅድ መታወቂያ ገዝተህ አልነበረም እንዴ! ታዲያ ለምን ትክዳለህ? አለና ስርቆቱን እንዴት እንዳከናወነ ሲጠይቀው ራሱን ሲያክ ቆየና እንዴት መሰለህ የሱፐር ማርኬቱ ባለቤት ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አካባቢ በአይሱዚ የተጫነ ሸቀጣሸቀጥ እንድናወርድለት ይጠራንና አንድ ሰባት ሆነን እየሮጥን ሄደን በፍጥነት እያወረድንለት እያለን እኔ በግሮሰሪው ውስጥ ተደብቄ እንድቀር የሆነ ነገር ገፋፋኝ ከዚያም በአንድ ባዶ ክርቶን ውስጥ ገብቼ ቁጭ ስልየሱፐር ማርኬቱ ባለቤት ሸቀጦችን ካስወረደ በኋላ አገር አማን ብሎ ለሠራተኞች ሂሳባቸውን ከፍሎ በሩንና መስኮቶችን በመዝጋት ሲሄድ እኔ ከሱፐር ማርኬቱ ውስጥ ቀረሁ::

በዚህ ሁኔታ ለተወሰነ ሰዓት ቆየሁና ሁሉም ወደ ቤቱ ገብቶ አካባቢው ፀጥ ሲል ከካርቶኑ ወጣሁና መብራቱን አብርቼ በሱፐር ማርኬቱ ውስጥ ያሉ ዕቃዎችን ስቃኝ በቀላሉ ሊያዙና ዋጋ ሊያወጡ የሚችሉትን በመሰብሰብ በካርቶን ውስጥ አድርጌ ልሸከመው ስሞክር በጣም ከባድ ሆነብኝና ቀንሸ በሌላ ካርቶን አድረግሁት:: ከዚያም መስኮቱን በውስጥ በኩል በመክፈት በቀላሉ ዕቃዎችን በካርቶን በመሸከም ወደ ሙሉዓለም የባህል ማዕከል አዳራሽ አጠገብ ካለው ፓርክ ውስጥ አስቀመጥሁና እንደገና ወደ ሱፐር ማርኬቱ በመመለስ ቀንሼ የተውሁትን ዕቃ እንደገና ተሸክሜ ስጓዝ አንድ ሰካራም አየኝና አንተ ሌባ ከየታባህ ዘርፈህ ነው የምትሄድ? ሲለኝ በመደናገጥ በደመነፍስ ወደ እሱ በመጠጋት ዝም እንዲል ሳስፈራራው እሱም በፈንታው ደንገጥ ብሎ እሽ! እሽ! ላግዝህ እንዴ! እያለ ሲንገዳገድ ጥዬው እግሬ አውጭኝ በማለት ፈጥኜ ከእሱ ራቅሁ:: ከዚያም ወደ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ከጎርፍ መሄጃው ቱቦ ውስጥ ወስጀ አስቀመጥሁት::

ይህ በዚህ እንዳለ ዕቃዎችን እንዴት መሸጥ እንዳለብኝ ቀደም ብዬ የማውቀውን አንድ ደላላ ሣማክረው ጨለምለም ሲል አምጣውና እንሸጠዋለን አለኝ:: በዚህም መሠረት የተወሰኑትን ዕቃዎች ውስጀ አስረከብሁት:: ከሦስት ቀናት በኋላ የሸጠበትን ገንዘብ እንዲሰጠኝ ስጠይቀው የምን ገንዘብ ነው በማለት ካደኝ:: እንዲያውም ይባስ ብሎ አንተ ሌባ ጠቁሜ እንዳላስይዝህ ከፊቴ ጥፋኝ በማለት አስፈራራኝ:: እኔም ምንም ማድረግ እንደማልችል በመገንዘብ ቀሪዎችን ዕቃዎች ባለሱቆች እንዲገዙኝ ስጠይቅ እሽ እንገዛሃለን ብለው ይዤላቸው ስቀርብ ፖሊሶችን አዘጋጅተው እጅ ከፍንጅ አስያዙኝ:: እኔም ለምን ብቻዬን እያዛለሁ በማለት ያን የካደኝን ደላላም እንዲያዝ አደረግሁት:: በማለት ለመርማሪው ፖሊስ ነገረው:: መርማሪውም እሽ እና መታወቂያውን እዚያ የጣልኸው ሌላ ሰው ሰረቀው ለማሰኘት ነው? በማለት ሲጠይቀው አይ! ሆን ብዬ አይደለም መታወቂያው የወደቀብኝ የሰበሰብሁትን እቃ በካርቶን ለመሸከፍ ዝቅ ቀና ስል ነው:: በማለት ተናገረ:: መራማሪው ፖሊስም መታወቂያውን እንዴት እንዳገኘው ሲጠይቀው:: ትንሽ አሰብ አድርጎ ገዝቸው ነው አለ:: ከየት ሲለው፣ መቼም ከቀበሌ አልልህ ያው ከሌቦች ነው:: በማለት አረጋገጠ:: ፖሊሱም ስለድርጊቱ አፈጻፀም የተለያዩ ጥያቄዎችን ሲጠይቀው ቆዩና እሱንም ወደ ሌላ ፖሊስ ጣቢያ ላከው::

ይህ በዚህ እንዳለ በእለቱ ስምንት ሰዓት አካባቢ ሣጅን ብርቱካንና ሙዝ ይዞልኝ መጣ:: እንደመጣ እንዴት ነው? ምን አዲስ ነገር አለ? በማለት ፖሊሱን ሲጠይቀው አሁን እንኳን ነገሮች ሁሉ እየተመቻቹ ይመስለኛል:: ምክንያቱም፣ በዝርፊያው ተግባር እሱ እንደሌለበት የሚያመላክቱ ፍንጮች እየታዩ መጠዋል::

ይቀጥላል!

## የኔ ሃሳብ

# እኛ እንዲህ እንላለን (አራት)

# አካዳሚያዊ ኢታማኝነትን (Academic Dishonesty) ልንታገል ይገባናል!

አበባው ይርጋ አዳሙ (ዶ/ር)
ትምህርትና ስነባህርይ ፋኩልቲ

### መግቢያ

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሚሰጣቸው የማሕበረሰብ አገልግሎቶችና በቅድመ-ምረቃና በድህረ-ምረቃ ፕሮግራም የሚሰጣቸው የተለያዩ የትምህርት ዘርፎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፉ መምጣታቸው እሰየሁ የሚያሰኝ ነው። በርዕይ ጥበብ 2017 እንደታወጀው ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በቀጣይ አስር ዓመታት ውስጥ በአፍሪካ ከሚገኙ አስር ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ለመሆን ጥረት እያደረገ ነው። ይህ ደግሞ የምርምር ባህል በዩኒቨርሲቲው ውስጥ እንዲሰርጽ ብሎም እንዲጎላ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። አስረጅ ብንባል በቂ ነው ባንልም ዩኒቨርሲቲው አንጻራዊ በሆነ መልኩ ቀደም ሲል ከነበረው በተሻለ መልኩ ለምርምር የሚውል ገንዘብ መመደቡን፣ የምርምር ስራ የሚያቀርቡ መምህራንን (ሁሉን በደፈናው ተመራማሪ ማለት ስለከበደን ነው) በተለያየ መልኩ ማበረታቱንና የተለያዩ ትምህርታዊ ስብሰባዎች (ኮንፍረሶች) እንዲካሄዱና በአንዳንዶቹም በሃገር ደረጃ ግንባር ቀደም ለመሆን የሚያደርገውን እንቅስቃሴ እንጠቅሳለን: : በዩኒቨርሲቲያችን እየተስፋፉ የመጡት ግን ከላይ የጠቀስናቸው አዎንታዊ ጉዳዮች ብቻ ሳይሆኑ አሉታዊ ጉዳዮችም ናቸው። እንደ እውቀት ተቋም ልናሳድገው የሚገባን ባህል ቢኖር በጥንካሬያችን መግፋትን ብቻ ሳይሆን ድክመታችንን አውቀን ማረምንም ጭምር ነው። ስለሆነም እኛ ዛሬ እድገታችንንና ጥሩ ገጽታችንን ከሚያጨልሙትና ድክመቶቻችን ናቸው ከምንላቸው መካከል አንዱ የሆነውን - አካዳሚያዊ ኢታማኝነት (academic dishonesty) - አንስተን እንዲህ እንላለን።

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ አካዳሚያዊ ኢታማኝነት (academic dishonesty) ማለት መምህራንና ተማሪዎች አካዳሚክ ሙያ የማይፈቅደውን (unethical) ነገር መፈጸም ወይም ሆኖ መገኘትን ይመለከታል። እንዲያው ለዚህ ጽሁፍ ግንዛቤ ሲባል ሃሳቡን ወይም ብያኔውን እንዲህ በአንድ ዓረፍተ ነገር ቋጨነው እንጂ ከዚህም በላይ ባብራራነው ነበር። አካዳሚያዊ ኢታማኝነት በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚገኝ ሲሆን ፍተሻውና ተጠያቂነቱ የሚላላባቸው ሃገሮችና ተቋሞች ግን ዋነኛ መጠለያዎቹ ናቸው። አንዳንዶች ይህንን አለማቀፋዊነት ባህርይውን ነገር ለማለዘቢያነትና ለሚሰሩት ስህተት ይቅር መባያነት ሲጠቀሙበት እናስተውላለን። ለምሳሌ፡- አንዳንድ መምህራንና ኃላፊዎች አካዳሚያዊ ኢታማኝነት ድሩን ሲያደራብን፣ ሲተበትበንና ወደፈለግነው የእውነትና የእውቀት ጎዳና እንደፈለግነው እንዳንጓዝ ሲያደርገን መፍትሄ ፈላጊ አካል ከመሆን ይልቅ ‹‹ይህ የኛ ብቻ ችግር ሳይሆን በሌሎችም ተቋማትና ሀገራት ያለ ጉዳይ ነው›› ይላሉ፤ ተማሪዎችም የመሰል ክፉ አስተሳሰብ ሰለባ ሲሆኑ ይስተዋላል። ለምሳሌ ‹‹ስርቆት እዚህ ብቻ ሳይሆን በየዩኒቨርሲቲው ያለ ነው፤ እኔ ብቻ ሳልሆን እነእከሌም በዚህ መልኩ ሰርተዋል፤ ሰርተውም ተመርቀዋል›› በማለት ይሞግታሉ: : ይህ የሆነና የሚሆንም ነው። ነገር ግን በመሰል ምክንያቶች ሊታለፍና ሊበረታታ ሳይሆን ሊታረምና ሊወገዝ የሚገባው አካሄድ ነው እንላለን: : እንደዚህ ዓይነት ጉዳዮችን ከወዲሁ ካልታገልን ‹‹prevalence and causes of academic cheating›› በሚል ርዕስ ጥናት አድርጊያለሁ ብሎ የምርምር ውጤት ያቀረበው መምህር ስራው ከሌሎች ስራዎች የተገለበጠ ሆኖ እንዳገኘነው ሁሉ አሳፋሪና ለማስተካከል ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅ መሆኑ አይቀሬ ነው። ደግሞስ ከሌሎች ተቋማትና ሀገራት መልካም ተሞክሮን እንጂ ስንፈትናን ድክመትን እንድንወስድ የሚያዘን ወይም የሚመክረን ማን ነው? የዛሬው ጽሁፍ ዋነኛ ዓላማችን በዩኒቨርሲቲያችን ውስጥ እየጎሉ (ወፌ ቆመች እየተባሉ) ከመጡ የአካዳሚያዊ ኢታማኝነት መገለጫዎች መካከል የተወሰኑ ነጥቦችንና ምክንያታቸውን በማንሳት የመፍትሄ ሃሳብ መሰንዘር ነው።

### 1. የተማሪዎች የምረቃ ማሟያ ጽሁፍ ስርቆት

በቅድመ-ምረቃና በድህረ-ምረቃ ፕሮግራም ውስጥ ባሉ የተለያዩ የትምህርት ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ተመራቂ ተማሪዎች ለዲግሪ ማሟያ የሚሆን ጽሁፍ (ፕሮጀክት) ያቀርባሉ: : ይህም ተማሪዎች በንድፈሃሳብ የተማሯቸውን እሳቤዎች መሰረት በማድረግና የምርምር ሙያ በሚፈቅደው መሰረት የሚያቀርቡት የምርምር ስራ ተብሎ ሊጠራ ይችላል። ዋነኛ አላማው (እንደየደረጃው የሚለያይ ቢሆንም) የምርምር ንድፈሃሳቦችን ተረድቶ በተግባር ማዋል በተማሪዎች ዘንድ ይበልጥ እንዲሰርጽ ወይም ችግር ፈቺ የሆነ ምርምር እንዲያካሂዱ ለማድረግ ወይም ሁለቱንም ለማሳካት ሊሆን ይችላል። አላማው የትኛውም ቢሆን ተማሪዎች የሚያቀርቡት ስራ የራሳቸው (ከሌሎች ያልተገለበጠ) ሊሆን ይገባል። ምክንያቱም የሌሎች ሰዎችን የምርምር ስራ ለመገልበጥ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም የማስተርስ ዲግሪ ትምህርት አያስፈልግምና ነው።

በዩኒቨርሲቲያችን ውስጥ የምረቃ ማሟያ ጽሁፍ ስርቆት (በቅድመ-ምረቃና በድህረ-ምረቃ) ከዚህ በፊት የታየ ቢሆንም እርምጃዎች ተወስደው ከመጥፋት ወይም ከመቀነስ ይልቅ በጣና ሃይቅ ላይ እንደሚታየው አረም በፍጥነት መስፋፋቱ እጅግ አሳሳቢ ይመስለናል። ለዚህም አስረጅ የሚሆኑንን ነጥቦች እናንሳ። አስረጅ 1፡- አንድ ተመካሪ ተማሪያችን የእኛኑ ስራ ለመመረቂያ ጽሁፉ በትልመ ጥናትነት (proposal) ያቀርባል። እኛም ለተመካሪያችን ያቀረበው ስራ የእኛ እንደሆነና ይህም ከፍተኛ ነውር እንደሆነ ነገርነው። ተመካሪውም ነገሩን አቅልሎ “It is ok. I can change it” አለን። ስለእሱ ስርቆት እኛ ተሳቀቅን፤ ስለእሱ ድፍረት እኛ አፈርን። ይህም፣ መሰል ተግባራት በተማሪዎች ዘንድ የተለመዱና እንደ መጥፎ ምግባር የማይቆጠሩ መሆናቸውን ለመረዳት አስቻለን። የሚገርመው ደግሞ ይህ ተመካሪያችን ስራችንን የገለበጠው በቀጥታ ሳይሆን ቀደም ሲል ገልብጦ ከተመረቀ ሌላ ተመራቂ ተማሪ መሆኑ ነው። አስረጅ 2፡- በያዝነው የትምህርት ዘመን በአንድ ፋኩልቲ ውስጥ አምስት የድህረ-ምረቃ ትምህርት ማሟያ ጽሁፎችን በውጭ ገምጋሚነት (external examiner) እንድንገመግም እንጠየቃለን። እንዲህ አይነት ስራዎች ተቋማዊ ግዴታን ለመወጣት ብሎም ሙያዊ ልምድን ለማዳበር ጥሩ አጋጣሚዎች ናቸውና በጸጋ ተቀበልን (ከተሞክሯችን እንደተገነዘብነው እንዲህ ዓይነት አጋጣሚዎችን ከገቢ አንጻር ብቻ የሚያዩ ፈታኞች የሉም ለማለት አንደፍርም)። ከዚህ ቀደም በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎችና በእኛም ዩኒቨርሲቲ የሰውን ስራ ወይም ሃሳብ እንደ ራስ ወጥ ስራ ማቅረብ (plagiarism) እየበዛ መምጣቱን ሰምተን ስለነበር በዚህ አጋጣሚ ይህንንም ለማረጋገጥ ፈለግን፤ የተሰጡንን የድህረ-ምረቃ የመመረቂያ ጽሁፎችን እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ አንበብን አስተያየት ሰጠን፤ ከዚያም ተመሳሳይ ስራዎችን ከድረ-ገጽ አወረድን፤ ከቤተመጻህፍትና ከሌሎችም ቦታዎች አመጣን፤ አየን፤ አዘን። አምስቱም ስራዎች በዚህ ሂደት ውስጥ ሲያልፉ አብዛኛው ክፍሎቻቸው ቀለውና የተማሪዎቹ ሳይሆኑ የplagiarism ውጤት ሆነው አገኘናቸው። እኛ ብቻ ሳንሆን ሌሎች የታተሩ ፈታኞችም መሰል ጉዳዮችን (ጉዳቶችን) ፈትሸው አገኙ። ይበልጥ የሚገርመው ደግሞ በተለያዩ ዓመቶች በተመሳሳይ ርዕስና ይዘት (ለማታለል በመሃል ከሚገቡ ማደናገሪያዎች በስተቀር) ሶስትና ከዚያ በላይ ተማሪዎች የማስተርስ ዲግሪ ሲሰጣቸው (ሲዘርፉ ማለት ሳይሻል አይቀርም) መመልከቱ ነው: : በዚህ መልኩ ለመመረቅ መሞከር በዩኒቨርሲቲያችን ውስጥ እንደ አሸን እየፈሉ ካሉት የአካዳሚያዊ ኢታማኝነት (academic dishonesty) መገለጫዎች አንዱ ነው።

ለዚህ ዋነኛ ምክንያቶችና ለመስፋፋቱ አስተዋጽኦ ያደረጉ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው? ለዚህ በርካታ ምክንያቶች ሊጠቀሱ ቢችሉም እኛ የሚመስለንንና ከተሞክሮ ያየናቸው የሚከተሉት ናቸው። 1ኛ) ተማሪዎች ምርምር አንድ የእውቀት መሸመቻና ወደፊት በስራ ዓለም የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ሳይንሳዊ በሆነ ዘዴ ለመፍታት የሚያስችል አማራጭ ሳይሆን ለመመረቅ ማሟላት ያለባቸው ግዴታ ብቻ አድርገው መመልከታቸው፤ 2ኛ) ትምህርቱን ሲጀምሩ ወይም ዋነኛ አላማቸው እውቀቱ ሳይሆን ወረቀቱ መሆኑ፤ 3ኛ) የምርምር እውቀት ማነስ (ይህ በስራቸው ላይ በግልጽ ይስተዋላል)፤ 4ኛ) የአማካሪዎች ግዴለሽነትና በርካታ ተማሪዎችን ማማከር ያመጣው ጫና፤ 5ኛ) ጥፋተኛ ሆነው በሚገኙ ተማሪዎች ላይ የሚወሰደው እርምጃ ለሌሎች ተማሪዎች በበቂ ሁኔታ አስተማሪ አለመሆን (ከፍተኛ የሚባለው እርምጃ ተማሪው ሌላ ርዕስ መርጦ ከእንደገና እንዲሰራ እድል መስጠት መሆኑን ልብ ይሉዋል)፤ 6ኛ) መሰል ስርቆቶችን ለማስቀረት የሚያስችሉ ጊዜያዊና ዘላቂ መፍትሄዎችን አለማስቀመጥ ናቸው።

እና ምን እናድርግ? 1ኛ) አሁን ያለው ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳየው ብዙ ተማሪዎች የምርምር ዘዴ እውቀታቸው አነስተኛ እንደሆነ ነው። የተሻሉ የሚባሉትም እውቀታቸው በአንድ ጎራ የከተመ ነው፤ ይህም ምርምሩ ምንም ይሁን ምን ቁጥር ካላስገቡ የምርምር ስራ የሰሩ የማይመስላቸው የቁጥር አብዮተኞችን ያፈራ ነው። ይህን ለማሻሻል በቅድሚያ ተማሪዎቻችን ለዚህ ስራ ስንቅ የሚሆናቸውን የምርምር ዘዴ በሚገባ እናስተምራቸው። ስናስተምርም እኛ የምንፈልገውንና የሆነውን ሳይሆን ስለምርምር ዘዴዎች የምናውቀውን

ወደ ገጽ 13 ዞሯል

# እንግዳችን

**የዚህ ወር እንግዳችን በዩኒቨርሲቲያችን በተለያዩ ክፍሎች ለረጅም ጊዜ አገልግለዋል፡፡ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ስለነበራቸው ቆይታና ተሞክሮ እንዲያጫውቱን ቃለ መጠይቅ አድርገንላቸዋል፡፡ ቃለ መጠይቁን እነሆ፡፡ መልካም ንባብ!**

ናይል፡- የናይል እንግዳ ለመሆን ፈቃደኛ ስለሆኑ በቅድሚያ እናመሰግናለን፡፡ በትውውቅ እንጀምር

ጕሼ፡- ስሜ ጕሼ መንግስቴ ካሳሁን እባላለሁ፡፡ እኔም ለናይል ጋዜጣ እንግዳ አድርጋችሁ ስለመረጣችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡

ናይል፡- ስለ ትውልድዎና ስለ አስተዳደግዎ ቢያጫውቱን?

ጕሼ፡- እኔ የተወለድኩት በሰሜን ጎንደር ዞን በለሳ ወረዳ ልዩ ስሙ ሐሙሲት በሚባል የገጠር አካባቢ በ1951 ዓ.ም ሲሆን ያደኩትም ከእናትና ከአባቴ ጋር ነው፡፡ አስተዳደጌም እንደማንኛውም የገጠር ልጅ በግብርና እና ከብት በመጠበቅ ነው፡፡

ናይል፡- ወደ ባሕር ዳር መቼ መጡ?

ጕሼ፡- ወደ ባሕር ዳር የመጣሁት በ1972 ዓ.ም ነው፡፡

ናይል፡- የትምህርት ሕይወትዎ ምን ይመስላል?

ጕሼ፡- በ1972 ዓ.ም ወደ ባሕር ዳር እንደመጣሁ ከመሰረተ ትምህርት ጀምሬ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ገብቼ እስከ ስምንተኛ ክፍል ነው የተማርኩት፡፡

ናይል፡- የትዳር ሕይወትዎ ምን ይመስላል?

ጕሼ፡- ያገባሁት በ1982 ዓ.ም ነው፡፡ ሶስት ወንድ ልጆች አሉኝ፡፡ በትዳሬ በጣም ደስተኛ ነኝ፡፡ ሚስቴ ለእኔ እናት እና አባቴ ማለት ናት፡፡

ናይል፡- ባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ መቼ ተቀጠሩ?

ጕሼ፡- ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በዚያን ጊዜ ኮሌጅ ነበር፡፡ የተቀጠርኩት በ1974 ዓ.ም መስከረም ወር በቋሚ ቅጥር በአትክልተኝነት ነበር፡፡ ኮሌጁ ከብት እርባታ ሲጀምር ከፎገራ ከብት እርባታ 17 የቁም ከብቶች ተገዝተው ሲመጡ እኔን ከአትክልተኞች መካከል አቶ በለጠ ተክሌ መርጠው በከብት ሕክምና ስልጠና ለ6 ወር ሰልጥኜ የከብቶችን ጤንነት ስንከባከብ ቆየሁ፡፡ ከዚያም በ1977 ዓ.ም የፓዊ ዘመቻ ነበር፡፡ እኔም ከዘመቻው መሄድ ፈልጌ ነበር፡፡ ነገር ግን ከብቶችን የሚንከባከባቸው ስለሌለ እኔን ከዘመቻው አስቀሩኝ፡፡ ከዚያም ሰራተኞችም ተማሪዎችም ከዘመቻው እንደተመለሱ በወቅቱ ዶ/ር ደምሴ ዲን ነበር፡፡ አቶ ወርቄ ደምሴ ደግሞ አስተዳደር ነበሩ፡፡ ይሄ ልጅ ወጣትም ስለሆነ ረዳት መካኒክ ሆኖ ወደ ትራንስፖርት ክፍል ሂዶ ቢሰራ ጥሩ ነው ብለው ስላሰቡ ወዲያው ካሳሁን ውዱ ከተባለ መካኒክ ጋር ረዳት መካኒክ ሆኜ እንድሰራ ደብዳቤ ደረሰኝ፡፡ ከዚያም የከብቶችን ማቴሪያል እንደ መርፌ፣ መድኃኒት ወዘተ… ያሉትን እቃዎች አረካክቤ ረዳት መካኒክ ሆንኩ፡፡ ወደ ስድስት ወር ገዳማ ረዳት መካኒክ ሆኜ እንደሰራሁ የጭነት መኪና ረዳት አደረጉኝ፡፡ በ1979 ዓ.ም ሁለተኛ መንጃ ፈቃድ አወጣሁ፣ በ1980 ዓ.ም ሶስተኛ መንጃ ፈቃድ፣ እንዲሁም በ1982 ዓ.ም አራተኛ መንጃ ፈቃድ አወጣሁ፡፡ ከዚያም ኮሌጁ የውስጥ እድገት ሲያወጣ በ1982 ዓ.ም መጨረሻ 180 ብር በዛን ጊዜ ትልቅ ደመወዝ ነበር በ180 ብር ደመወዝ ፈተናውን አለፍኩና የከባድ መኪና ሾፌር ሆንኩ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በሾፌርነት እያገለገልኩ እገኛለሁ፡፡

ናይል፡- በሕይወትዎ የሚወዱት ነገር ምንድን ነው? የሚጠሉትስ?

ጕሼ፡- በሕይወቴ የምወደው ነገር መጫወት መቀለድ ደስ ይለኛል፡፡ በሕይወቴ በጣም ደስተኛ ነኝ፡፡ ከማንም ጋር ሥራ ላይ ሆኜ ልቀልድ እችላለሁ፡፡ ሥራ ከታዘዝኩም ቀድሜ እገኛለሁ እንጅ ሥራን ማጓተት አልፈልግም፡፡ ጭቅጭቅ አልወድም፡፡ ዋናው እኔ ባለኝ ነገር ፈጣሪን ተመስገን ነው የምለው፡፡

ናይል፡- በዩኒቨርሲቲው ባሳለፉት የሥራ ዓመታት ውጤታማ ነኝ ብለው ያስባሉ? እንዴት?

ጕሼ፡- አዎ ውጤታማ ነኝ፡፡ አንድ ሹፌር የያዘውን ንብረት ሳይወቀስ ገደል ሳይሰድ ያለአግባብ በመንግስት ንብረት ሳይወቀሱና ሳይባክን ይህን ያክል ዘመን መሥራት ቀላል አይደለም፡፡ እኔ የመንግስትን ንብረት ያለአግባብ አልጠቀምም፡፡ በሕይወቴም አድርጌው አላውቅም፡፡ ወደፊትም አላደርገውም፡፡ ከሰዎች ጋር የሚያጋጨኝ ነገርም ይህ ነው፡፡ ሥራ ከሆነ ሥራ ነው ከዛ ውጭ የመንግስትን ንብረት ለግሌ አልጠቀምም፡፡ አስተዳደርና ልማት በነበረበት ወቅት ዶ/ር ገ/እግዚአብሄር በመንግስት ንብረት ጥብቅ እንድሆን፣ ዋሽቶ መኖር እንደሌለብኝና በሥራዬ ጠንካራ እንድሆን ያደረገኝ እሱ ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚ ዶ/ር ገ/እግዚአብሄርን ማመስገን እፈልጋለሁ፡፡ ሥልጣንን በአግባቡ የሚጠቀም ሰው ያስደስተኛል፡፡ ክፋተኝነት፣ ጕጠኝነትና ተንኮለኝነት አልወድም፡፡ ሰው መወደድ ያለበት በሥራው ነው፡፡ ሰው መጠላት ያለበት በጅልነቱ ነው የሚል አቋም አለኝ፡፡

ናይል፡- በዩኒቨርሲቲው ባሳለፏቸው የሥራ ዓመታት ቅር የሚሎት ነገር ምንድን ነው?

ጕሼ፡- በአዲሱ መዋቅር ላይ ሥራ የተሰራው በወረቀት ላይ ያተኮረ ስለሆነ ተጠቃሚ አይደለሁም፡፡ ምክንያቱም እኔ ያለኝ የብዙ አመት የሥራ ልምድ እንጅ ወረቀት የለኝም፡፡ የሥራ ልምድም ባለመታየቱ ተጕጅ ነኝ እላለሁ፡፡ ከመንግስት ከሚመጣው ጭማሪ በስተቀር በዩኒቨርሲቲው በመጣው የደረጃ እድገትም ይሁን የገንዘብ ጭማሪ አልተደረገልኝም፡፡ በዚህ ቅር ብሎኛል፡፡ ከወረቀት ይልቅ



ጕሼ መንግስቴ ካሳሁን

የሥራ ልምድ ይጠቅማል የሚል አመለካከት ስላለኝ ነው፡፡

ናይል፡- በሥራ አለም የማይረሱት ገጠመኝ ካለዎት?

ጕሼ፡- በሕይወቴ ያዘንኩበት ጉዳይ አንድ ጊዜ የአዳር ሥራ ስንሰራ አንድ የመኪና ጕማ ተፈቶ ተገኘ እና ተከሰስን፡፡ ሌሎች ሾፌሮች ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸው ጕሽ ግን የጕማውን ዋጋ ይክፈል ተባልኩ፡፡ ከዚያም እኔ አዲስ አበባ ሲቪል ሰርቪስ ሄጀ ከሰስኩ፡፡ ዩኒቨርሲቲው ተጠየቀ፡፡ ጕሽ ለመውሰዱ የሶስት ምስክሮች ቃል እና የፈረሙበትን አምጡ ተባሉ፡፡ አራት ጊዜ ተመላልሼ በአምስተኛው ውሳኔውን ሽረነዋል ተብሎ ሲቪል ሰርቪስ ወሰነልኝ፡፡ ገንዘብ የቆረጣችሁበት ካለም ይመለስለት ተባልኩ፡፡ የተቆረጠብኝ ገንዘቤም ተመለሰልኝ፡፡ እንዲህ ዓይነት ነገር በሕይወቴ አጋጥሞኛል አልረሳውም፡፡ እኔ አብሬ ከሌባ ጋር አልተባበርም፡፡ የሚያስደስተኝ ደግሞ እኔ በምሰራው ሥራና በሕይወቴ ባለኝ ነገር ፈጣሪዬን እያመሰገንኩ ሁሌም ደስተኛ ነኝ፡፡

ናይል፡- በፊት ከብት እርባታው ላይ እያሉ የገጠመዎት ነገር አለ ይባላል እስቲ ያጫውቱን?

ጕሼ፡- ፔዳ የቅርጫ ከብት ይታረድና ከመዘጋጃ ቤት ጥቆማ ደርሷቸው ሕገወጥ ከብት እየታረደ ነው ተብሎ ሥጋውን ሊቀብሩ ይመጣሉ፡፡ በወቅቱ ሰውዓለም አድገህ የተባለች የሰው ኃይል አስተዳድር ነበረች፡፡ 6 ወር የሰለጠነ ባለሙያ አለን ተባለ፡፡ የት ነው የሰለጠንክ ተባልኩ፡፡ ከብት ሕክምና አልኩ፡፡ ያንን ሊቀበር የነበረውን ሥጋ አትርፌዋለሁ፡፡

ናይል፡- ከብት እርባታው ላይ ሲሰሩ ሌላም አስቂኝ ገጠመኝ አለዎት ይባላል እስቲ ስለእሱም ይንገሩን?

ጕሼ፡- ከብት ቤት ስሰራ ጥጃ ጠባቂ ልጅ ነበርና ይህ ልጅ ወባ ይታመማል፡፡ ለጥጆች ወይም ለእንቦሶች የምሰጣቸውን ፔንሲሊን ሁለት ሲሲ እንኳን አትሞላም ልጁን መርፌ ወጋሁት፡፡ ከጥቂት ሰዓት በኋላ ተኝቶ ሲነሳ እንዴት ነው አልኩት፡፡ አሁን ድኛለሁ አለ፡፡ ይሄው ከዛ ወዲህ መድኃኒቱ ነው መሰል ተስማምቶት ወፍሮ ይታያል፡፡

ናይል፡- ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ምርጥ ዩኒቨርሲቲ እንዲባል ምን አስተዋፅኦ ያደርጋሉ?

ጕሼ፡- እንደ እኔ ምኞት ቢሆን ኖሮ ዩኒቨርሲቲው በመጥፎ እንዲነሳብኝ አልፈልግም፡፡ ግን ያለቆቻችን መፈራረቅና የጥቂት አለቆች ብልሹ አሰራራቸው እኔ ራሱ ከተማ ወጥቼ ስሰማ አፍራለሁ፡፡ ጅል ወሬ ስሰማ እንዲህ ተደረገ ሲባል ያሳዝነኛልም አፍራለሁም፡፡ ምክንያቱም ለረጅም ጊዜ ቆይቼበታለሁ፡፡ እኔ እንደኔ ቢሆን እንደዚህ አይነት አለቆች ጥሩ ምክር እንዲሰጣቸው ቢደረግ፡፡ ለምን ቢባል እነሱ እኛን መምከርና ማረም አለባቸው፡፡ በከተማ ወጥተሽ የዩኒቨርሲቲው ስም ሲጠፋ ስትሰሚ ደግሞ በጣም ያሳፍራል እኔ አዝናለሁ፡፡ በመኪና አያያዝ ደግሞ ማንም በየሜዳው ሲማርበት ሳይ፣ በየደጃፉ የዩኒቨርሲቲው አርማ ያለበት መኪና በየግለሰቡ ማድቤት ቆሞ ሲታይ ይህ

ወደ ገጽ 9 ዞሯል

# ክፉ አመል!!

(በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ)

በሂሩት አድማሱ
የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነጽሁፍ ት/ክፍል - የስነጽሁፍ መምህርት
nanihira@gmail.com

ምንም ነገር አይቀረውም:: ያገኘውን ነገር በማታለል ከሰዎች ይወስዳል:: የወሰደውን በሙሉ ግን በአንድ ነገር ላይ ብቻ የሚያውለው ነው የሚመስለው፤ሲበዛ ወፍራም በመሆኑ ለምን እንደሚያውለው መገመት አያቅታችሁምና ግምቱ ለእናንተ ለአንባቢዎች ይሁን:: አመለኛው ይባላል:: ኒና ከጓደኞቹ ጋር ተቀምጦ በአጠገባቸው ሲያልፍ ሲያዩት ‹ክምር የፈጀ ዝንጀሮ ይመስላል› እያሉ ይሳሳቃሉ:: ማኩረፉን ሳይሆን የሰውነቱን መቆለል እያዩ:: በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የተቀጠረበት የሙያ መስክና የትምህርት ደረጃውን የሚያውቅ ያለ አይመስልም:: ከተቀጠረበት ሙያ ይልቅ የሚታወቅበት ሌላ ሙያ አለው:: ሰዎችን በማጭበርበር የረባም ይሁን ያልረባ አንድን ነገር መውሰድ:: ምን አለፋችሁ ይህ ተግባሩ ሱስ ሆኖበታል፤ የተነቃበት ሲመስለው ለጥቂት ጊዜ ይርቅና ሲረሳለት ደግሞ ተመልሶ ይመጣል:: የሚገርመው የሚያታልለው ነገር አለማጣቱ ነው::

ኒና ከአመለኛው ጋር የተዋወቀው ተማሪ እያለ ነው:: ያኔ ተማሪ እያለ ከብዙሃን ተማሪዎች ጋር ምን አንጋጋህ እኔ ሁለት ተማሪ የሚኖበትን ዶርም ልስጥህ ብሎት ለማስፈጸሚያ በተማሪ አቅሙ 50 ብር ተቀብሎታል ምንም ባያደርግለትም:: በተማረበት ተቋም ስራ የመያዝ ዕድል ያገኘው ኒና አመለኛው በሚሰራበት ተቋም ውስጥ መስራት በጀመረባቸው ጥቂት ወራት ውስጥ አንድ የማታለል ሙከራ ተደረገበት:: የተቋሙ ሰራተኞች ከደሞዛቸው በየወሩ ተቆራጭ በማድረግ የሚያጠራቅሙበት ሲፈልጉ ደግሞ የሚበደሩበት የብድርና ቁጠባ ማህበር አላቸው:: እናም አንድ ቀን ጥልቅ ትውውቅ እንዳላቸው በሚመስል አቀራረብ ሰላምታ አቀረበለትና የፈጠራ ታሪክ ነግሮት ከቁጠባው ብር እንዲበደርለት ጠየቀው:: ምስኪን አዲስ ተቀጣሪ! አዘነለትና ብበደርለትና ለጊዜው ችግሩን ቢወጣ ብሎ አሰበለት:: ሰባት መቶ ብር! ለአዲስ ተቀጣሪና በወቅቱ በነበረው የደሞዝ መጠን ብዙ ብር ነበር:: ኒና ይመልስ አይመልስለት ሳይመረምር ለማበደር ሳያቅማማ ወደ ብድር ተቋሙ ጎራ አለ:: የሆነው ሆኖ ቁጠባውን የተቀላቀለበት ጊዜ ስድስት ወር ስላልሞላ መበደር አልቻለም:: በዚህ ምክንያት ከመበላት ዳነ:: በኋላ ስለተበዳሪው አዝኖ ለነባር ጓደኞቹ ቢያጫውታቸው በግቢው ውስጥ የለመደ ተበዳሪና የተበደረውን መልሶ የማያውቅ ሰው እንደሆነ ተገለጸለት::

በሌላ ጊዜ የኒና እጣ በሴት ጓደኛው ላይ ደረሰ:: በጣም የቸኮለ ግን በእጁ ብር ያልያዘ እንደሆነ በመግለጽ ብር እንድታበድረው ጠየቃት፤ የዋሕ ሰናይት ያለኝ መቶ ብር ነው በጣም ከቸገረህና ከፈለከው ግን እንካፈለው እንደሆነ እንጂ ሌላ የለኝም አለችው:: አላመነታም ከኪሱ አርባ ብር ሰጥቷት መቶው ይዞ እብስ አለ:: አልተመለሰም:: ሲያያት ይሸሻት ጀመር:: ነገሩን ሰናይት ለኒናና ለሌሎች የስራ ባልደረቦቿ ነግራቸው ተሳሳቁበት:: እንደውም አንዱ ጓደኛቸው ‹መልስ መቀበልሽ ብሎ አፌዘባት› ተራው ቀጥሎ ሊደርሰው::

ከጥቂት ቆይታ በኋላ ይኸው አመለኛ ወደ ተረኛው የነኒና ጓደኛ አመራ «ወይኔ የሰናይት እህት ራሷን ስታ ወድቃለች::» ደጉ ደነገጠ:: «ምን ሆና የት ነች?» ጥያቄውን አዝጎደጎደ፤ መልስ ከመስጠት ይልቅ መፍትሔ ያለውን መቀባጠር ቀጠለ:: «ባጃጅ ጠርቻለሁ:: ብቻ ብር አልያዝኩም::» ደጉ ኪሱን ዳበስ አድርጎ ያገኘውን ብር አፈፍ አደረገና ሰጠው:: ልክ ብሩ ከጁ ሲወጣ ትዝ አለው አመለኛው እንደሆነ፤ ወዲያው ብሬን አምጣ ሊለው አሰበና ምን ተፍረቱን ዝም አለ:: ብዙም ሳይቆይ ሰናይትን አገኛት፤ እህቷን ጠየቃት:: የሰናይት እህት እንኳን ራሷን ልትስት ራሷንም አላመማት፤ወይ ማታለል!!

በሌላ ጊዜ በሌላኛው የግቢው ህንጻ የሚገኝ አንድ የሂሳብ መምህር የዕለት ተግባሩን አስተምሮ ሻይ ልጠጣ በሚል ጋዋኑን ቢሮው አውልቆ ሲመለስ በአመለኛው አይን ውስጥ ይገባል:: ጥሩ ዕድል ነበር ለአመለኛው፤ መራቁን ሲያይ ወደ ወጣበት ቢሮ ይሄድና የተላከ በማስመሰል ጋዋኑን እንደጠየቀ ቢሮው ውስጥ ላለው ሌላ መምህር ይነግረዋል:: ልብ ያላለው መምህር ጋዋኑን እንዲወስድ ይጠቁመውና ወደ ስራው ትኩረቱን ይመልሳል:: ሻይ ቤት የሄደው መምህር ሲመለስ ጋዋኑ የለም፤ አላስተዋለውም ነበር:: ቢሮው ውስጥ የተቀመጠው መምህር ግን «ያለወትሮህ ጋዋንህን አስልከህ ማስወሰድህ ለምነው?» ብሎ ይጠይቀዋል:: በጥያቄው ግር ያለው መምህር ‹‹የምን ጋዋን?›› ብሎ ግራ ይጋባል:: ባይኑ ካስቀመጠበት ሲፈልግም ያጣዋል:: ከዚያ ቀን በኋላ ጋዋኑን ባለቤቱ ሊለብሰው አልቻለም፤ እንደወጣ ቀረ! አልተመለሰም:: በኋላ የደረሰበት ሲጣራ ባለው ልዩ የሂሳብ ምልክት አማካኝነት ልኳንዳ መታየቱ ተነገረ፤ ስጋ የሚሸጥ ሰው ለብሶት:: አይገርምም ትላላችሁ!?

> **ከዚያ ቀን በኋላ ጋዋኑን ባለቤቱ ሊለብሰው አልቻለም፤ እንደወጣ ቀረ! አልተመለሰም:: በኋላ የደረሰበት ሲጣራ ባለው ልዩ የሂሳብ ምልክት አማካኝነት ልኳንዳ መታየቱ ተነገረ፤ ስጋ የሚሸጥ ሰው ለብሶት:: አይገርምም ትላላችሁ!?**

የአመለኛው ክፋት ጠይቆ በመውሰድ ላይ ብቻ የተመሰረተ አለመሆኑ ነው:: ክፍት ቢሮ ሲያገኝ፣ ተጸድቶ አየር እንዲገባው የተከፈተ በር ካየ ሰተት ብሎ ይገባል፣ እጁ የያዘለት ይዞ ይወጣል፣ እንዳዋጣው ይሸጠዋል:: መጽሐፍ፣ ደብተር፣ እስኪሪቢቶ፣ ዳስተር፣ ማርከር፣ እስቴፕለር መምቻ፣ የስቴፕለር ሽቦ፣ ጋዋን ብቻ ያገኘውን ከመውሰድ ወደኋላ አይልም::

አንድ ጊዜ ደግሞ እንዲሁ ስለአመለኛው ጥናት ማድረግ የያዘው ኒና አንዳንድ መረጃዎችን ይዞ አንድ ሁለት ቢሮዎች ጎራ አለ:: ከዚሁ ከአመለኛው ጋር የተያያዘ የሚገርም ታሪክ አገኘ:: ታሪኩ የአንድ የት/ክፍል ጸሐፊ የደረሰባት ነው:: በወቅቱ ለመምህራን ሊታደሉ የተዘጋጁ ሲቲከሮች፣ ማስታወሻ ደብተሮች፣ ማርከሮችና እስኪሪቢቶዎች ጸሐፊዋ ፊት ለፊት ካለው ጠረጴዛ ላይ ተሰድረዋል:: አመለኛው እግር ጥሎት ከዚያ ቢሮ ከተፍ ይላል:: ከሰላምታው አስከትሎ ስቲከር ልውሰድ? የሚል ጥያቄ ሰነዘረ:: ጸሐፊዋ አመሉን ታውቅ ስለነበር በጥርጣሬ አይንና በእሺታ መንፈስ አስተናገደችው:: የጠየቀውን ጨምሮ ካልጠየቀውም ከአይነት ከአይነቱ ጠረጴዛ ላይ ከተደረደሩት እንደ ብፌ ምግብ አንድ አንድ ማንሳቱን ቀጠለ:: ይሄን ጊዜ ትዕግስት ያጣችው ጸሐፊ «ኧረ በፈጠረህ በመጨረሻ እኔን እንዳትወስደኝ ፈራሁ::›› ያለችው ከሁሉም ታሪክ አስፈጋጊ ታሪክ ነው:: ነገሩ ቢያበሽቅም::

የአመለኛው ሌላው አመል ደግሞ የተረሳለት ሲመስለው ዙሩ መድገሙ ነው:: ከመጀመሪያው ዙር ማታለል የተረፈው ኒና ነገሩ ከተረሳሳ በኋላ ሁለተኛ ዙር ደረሰው:: ባሳለፍነው ሳምንት ውስጥ ነው:: በጣም ተመስጦ ኮንፒውተሩ ላይ እየሰራ ሳለ አመለኛው መጣ:: የናኒ አዕምሮ በቅጽበት ማንነቱን ከማስታወስ ይልቅ ለሚጠይቀው ጥያቄ አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት ወደ ትኩረቱ ለመመለስ ቸኩሎ ነበር::

«ኒና ወንድሜ እንዴት ነህ? ሰላም ነው?»

« እ እ ... ሰላም»

«እህቴ እናንተ ዲፖርትመንት ለመማር ተመዝግባ ነበር:: የመግቢያ ፈተና ይሰጣል እና በምን ዙሪያ ንባብ ታድርግ?» በርግጥ ኒና በተጠየቀው መስክ ልዩ ስልጠና የለውም:: የሚገምተውን አንዳንድ ነጥቦች ግን ከመናገር ወደ ኋላ አላለም::

«አሁን የነገርከኝ በሶፍት ኮፒ ይኖርሃል?» አለው:: እንደሌለው በመመለስ ለበለጠ መረጃ ሌሎች የስራ ባልደረቦቹን እንዲጠይቅ ሌላ ቢሮ ጠቆመው:: ፍላጎቱ የጠየቀው ጉዳይ አልነበረም ፤ ምናልባትም ሲዲ እና ጠረጴዛው ላይ ያለው እሽግ የነጭ ሰሌዳ ላይ መጻፊያ ማርከር እንጂ፤ ጥያቄው ቀጠለ::

«ይቅርታ ፕረዘንቴሽን ስላለብኝ የነጭ ሰሌዳ ማርከር ታውሰኛለህ?» ይህን ጊዜ ኒና ዓይኑን ጠረጴዛው ላይ አድርጎ ከታሸገው አንድ አውጥቶ ለመስጠት ገና ሲያስብ፤ ‹‹አመሰግናለሁ›› ብሎ እሽጉን ይዞት በጥድፊያ አፈትልኮ ወጣ:: በጓደኞቹ እና በሌሎች የሙያ ባልደረቦቹ የደረሰው ልዩ ልዩ የመታለልና የመጭበርበር ስራ ሳይበቃ..... ሁለተኛ ዙር የደረሰው ኒና ተገረመ፣ ተናደደ፣ ተበሳጨ:: ወዲያው አንድ የት/ክፍሉ ባልደረባ መጥቶ አመለኛው ምን ይዞ ሄደ ብሎ ጠየቀው እየሳቀ የነጭ ሰሌላ ማርከር ብሎ መለሰለት:: የበሸቀው ሌላኛው ባልደረባ እሱ ቢሮ ጨርሶ እንደማያስገባው ነገረውና ይበልጥ አስገረመው::

በጥቂቱ ያልታመነ እንደሚለው ትልቁ መጽሐፍ በጥቃቅ የማታለል ስራ ላይ የተሰማራው አመለኛ ትልልቅ ነገሮችን ቢያገኝ የሚምር አይመስልም:: ጥቃቅን የተባሉት ነገሮችም ቢሆኑ ትልቅ የእምነት ክህደት የተደረገባቸው ናቸው:: አንድ ቦታ ነው የምንሰራው ብለው ያመኑትን ሰዎችን እምነት ሽጦ በልቶ ነው እየደጋገመ የሚያታልላቸው:: የአመለኛው ያልተሰሙ እና በሱ የተሰሩ ሌሎች ከዚህም ገነን ያሉ ገድሎች እንደሚኖሩት ጥርጥር የለውም::

በቅርብ ጊዜ በተደረገ የሰራተኞች ድልደላ አመለኛው የሚሰራበትን ክፍል ቤተ መጽሐፍት ሆኗል:: ነገሩ ስሜት ቆረቋሪ ነው:: ጥያቄም ያጭራል:: ለመሆኑ መጽሐፍቱ ተርፈው ይሆን? ወይንስ በማይረባ ዋጋ ተሸጠው አልቀው ይሆን? ይህንን ማወቅ ከተራኪው አቅም በላይ ነውና ልብ እንዲባልለት ይፈልጋል:: ግን እውነት እንዲህ አይነቱ አመል ክፉ አመል እንጂ ምን ይሉታል?

# የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ እና የንግዱ ማሕበረሰብ አጋርነት ለተሻለ እድገት

በታድዬ አስማረ

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለባሕር ዳር ከተማ እድገትና ሥራ ፈጠራ ያለው ሚና ከፍተኛ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ለምሳሌ በልማት በኩል በከተማው አራት አቅጣጫዎች ያስገነባቸው የዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ግቢዎች ለከተማዋ እድገት ከፍተኛውን ድርሻ ይዟል፡፡ በሰው ኃይል ልማትም በመደበኛው መርኃ ግብር ተማሪዎችን ተቀብሎ ከሚያሰለጥናቸው በተጨማሪ በማታው፣ በክረምትና በርቀት መርኃ ግብሮች የአካባባውን ማህበረሰብ ተቀብሎ እያሰለጠነ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በመደበኛ መርኃ ግብር እድሉን ያላገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች እንደዚሁ በዩኒቨርሲቲው ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛል፡፡

በሥራ ፈጠራም ቢሆን በዩኒቨርሲቲው ተቀጥረው ከሚሰራው ማሕበረሰብ በተጨማሪ ለከተማዋ ነዋሪዎች የሥራ እድል በመሆን ሀብት እንዲያፈሩ በማድረግ እገዛ እያደረገ ይገኛል፡፡ ለዚህ ማስረጃ በከተማዋ አራቱም አቅጣጫ ባሉ ግቢዎች አካባቢ የሚኖሩ የንግዱ ማሕበረሰብ የተለያዩ የንግድ ሥራዎችን በመክፈት ለተማሪው አገልግሎት ከመስጠት ባሻገር ሀብት እያፈሩ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተማሪዎች በከተማዋ የተለያዩ ቦታዎች በሚዘዋወሩበት ወቅት ለተለያዩ አገልግሎቶች ወጭ በማድረግ ለንግዱ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረጉ እንደሆነ ይታመናል፡፡

ተማሪዎቹ ለባጃጅና ለታክሲ ወጭ ከማድረግ አንስቶ ለሻይ ቡናም ሆነ በምግብ ቤቶች እና ሆቴሎች በሚሰጡ አገልግሎቶች እየተጠቀሙ ይገኛሉ፡፡ የአልባሳት ግዥም ቢሆን ተማሪዎቻችን የአልባሳቶቻቸውን ፍላጐት የሚያሟሉት በባሕር ዳር ከተማ ከሚገኙ የአልባሳት ሱቆች መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዩኒቨርሲቲያችን በመደበኛው መርኃ ግብር ብቻ ከ20 ሺህ ተማሪዎች በላይ እየተማሩ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም የተማሪዎችን ወጭ በአማካኝ የቀን ወጭ ብር 10.00 ቢሆን (የክረምት፣ የማታና የርቀት ተማሪዎችን ሳንጨምር) በ20 ሺህ የተማሪ ቁጥር ብናበዛው ሁለት መቶ ሺህ ብር ከተማሪዎቻችን ይገኛል ማለት ነው፡፡ ይህ በወር ሲታሰብ ደግሞ ተማሪዎቻችን ከብር 6 ሚሊዮን በላይ ወጭ በማድረግ በከተማዋ እድገትና አስተዋፅኦ እያደረጉ ይገኛል፡፡ የክረምትና የርቀት ተማሪዎችም ቢሆን ዩኒቨርሲው ጥሪ ባደረገላቸው የጊዜ ሰሌዳ ወደ ከተማዋ በመጡ ጊዜ የሚያደርጉት ወጭም ከፍተኛ ነው፡፡

ዩኒቨርሲቲው ከተማዋ ደረጃዋን የጠበቀች በማድረግ ረገድም በአራት አቅጣጫ የመሠረተ ልማት ግንባታ እያካሄደ ይገኛል፡፡ በቅርቡም የፖሊ-ፔዳን መስመር ማስተርፕላን አሠርቶ ወደ ተግባር ለመግባት በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል፡፡ የፖሊ ፔዳ የተቀናጀ ማስተር ፕላን እውን ሲሆን ደግሞ ምን ያህል ሥራአጥ ወገኖቻችንን የሥራ ባለቤት ሊሆኑ እንደሚችሉ ሲታይ የዩኒቨርሲቲው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡ ለግንባታው የሚያስፈልጉ የግንባታ ቁሳቁሶችን ለማሟላት ደግሞ የንግዱ ማህበረሰብ ድርሻው የጎላ ነው፡፡ የነጋዴ ማህበረሰብም ከላይ በተጠቀሱት የንግድ እንቅስቃሴዎችም ሆነ ከሌሎች አዳዲስ በሚፈጠሩ የንግድ እንቅስቃሴዎች የበለጠ ተጠቃሚ የሚያደርገው ይሆናል፡፡

በመሆኑም ከዩኒቨርሲቲው እድገት ተጠቃሚ እየሆነ የሚገኘውን የንግዱ ማህበረሰብ ከዩኒቨርሲቲው ጋር እንዴትና በምን መልኩ አብሮ መስራት እንዳለበት ለመወያየት በቅርቡ ለንግዱ ማሕበረሰብ ጥሪ ተላልፎ ነበር፡፡ በተለይ የኢንፎርሜሽንና ስትራቴጅክ ኮሙኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ኃላፊነቱን ወስዶ ጥሪውን ማከናወኑ ይታወሳል፡፡ በተለይ ከዩኒቨርሲቲው ጋር በቀጥታ ከሚገናኙት መካከል የሸቀጣሸቀጥ፣ የምግብ ውጤቶች አቅራቢዎች /ጥራጥሬ፣ ሸንኩርት፣ ድንች፣ ጤፍ እና የመሳሰሉት/፣ የህትመትና ማስታወቂያ ድርጅቶች፣ የፅህፈት፣ ኤሌክትሮኒስ፣ ፈርኒቸርና የህንፃ ግንባታ ማሳሪዎች አቅራቢዎች በቀጥታ ጥሪው እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ ነገር ግን የንግዱ ማህበረሰብ ጥሪውን አክሮ አለመምጣቱ ዩኒቨርሲቲውን ያሳዘነ ጉዳይ ነው፡፡

የውይይት መድረኩ ለዩኒቨርሲቲውም ሆነ ለንግዱ ማህበረሰብ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው በበላይ አካላት ታምኖበት ነበር የተዘጋጀው፡፡ ዩኒቨርሲቲው በንግዱ ማህበረሰብ የሚነሱ የመልካም አስተዳደርና አሰራር ግድፈቶች /ተግዳሮቶች/ እና ጥንካሬዎች ላይ ተወያይቶ ግድፈቶችን ደረጃ በደረጃ ለመቅረፍ እንዲችል እና በጥንካሬው እንዲገፋበት ያግዛል እንዲሁም በንግዱ ማህበረሰብ በኩል ያለውን የአሠራርና የሥነ ምግባር ግድፈቶች /ተግዳሮቶች/ በመፈተሽና ጥንካሬዎች ላይ በመወያየት ከዩኒቨርሲቲው ጋር መልካም ግንኙነት እንዲፈጠር ለማድረግ በሚል መነሻ ሀሳብ የውይይት መድረኩ እንደተዘጋጀ ለንግዱ ማሕበረሰብ የተላከው የጥሪ ደብዳቤ ይገልፃል፡፡ ነገር ግን ይህን እድል ግን ሳይጠቀሙበት መቅረቱ ዩኒቨርሲቲውን አሳዝኗል፡፡ አሁንም ቢሆን ዩኒቨርሲቲው ከንግዱ ማህበረሰብ ጋር በዩኒቨርሲቲው የአሠራር ሂደትና አጠቃላይ እንቅስቃሴ መድረክ ከፍቶ ለመወያየት ከፍተኛ ፍላጐት ያለው በመሆኑ የንግዱ ማህበረሰብም ወደፊት ዩኒቨርሲቲው በሚያዘጋጀው የጋራ መድረክ ላይ ተሳታፊ በመሆን ለዩኒቨርሲቲም ሆነ ለከተማዋ እድገት አጋርነታቸውን እንዲያሳዩ ዩኒቨርሲቲው ጥሪውን ያቀርባል፡፡ በጋራ ለማደግ በጋራ መስራት ተገቢ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው በጋራ እንስራ ይላል!!!

# የዩኒቨርሲቲው የ2007 ዓ.ም የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ክንውን ባጭሩ ሲዳሰስ

በታድዬ አስማረ

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲን የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለማድረግ የተያዘውን ራዕይ ለማሳካት የዩኒቨርሲቲው ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት በዋናነት በምርምር ሥራዎች ላይ በማተኮር በበጀት ዓመቱ ያከናወናቸውን ተግባራት ለዩኒቨርሲቲው ማሕበረሰብ አስገምግሟል፡፡

ዩኒቨርሲቲው አስራ ሶስት የምርምር ማዕከላትን በማቋቋም ምርምር በማካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ የተለያዩ የምርምር ውጤቶች በጆርናል ታትመው እንዲወጡ በማድረግ እንዲሁም ሌሎችን ለጆርናሎች ተልከው እንዲታተሙ ከፍተኛ ስራ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

ካለፈው የበጀት ዓመት የቀጠሉና በተያዘው በጀት የተጠናቀቁ እንዲሁም በተያዘው በጀት እቅድ የታቀዱና በቀጣይ አመት የሚጠናቀቁ የምርምር ሥራዎች እንዳሉ ተገልጿል፡፡ በተያዘው የበጀት ዓመት የሚጠናቀቁ የተወሰኑ ምርምሮችን ወደ ማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮጀክቶች በመለወጥ ማሕበረሰቡ ጋር እንዲደርሱ ለማድረግ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው፡፡ እነዚህ የምርምር ማዕከላት የምርምር ሥራዎቻቸውን በተገቢው መንገድ እንዲያካሂዱ ሙከራዎችን በማደረጃትና በማስፋፋት ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማሪ ምርምር ማዕከላቱን ለማጠናከር ቁልፍ ተግባር ለማዕከሉ የሰው ኃይል ማሟላትና የተመራማሪዎችን አቅም መገንባት ነው፡፡ በመሆኑም ለማዕከላቱ ተመራማሪዎች እንዲሟሉ የተደረገ ሲሆን የተወሰኑት ተመራማሪዎች የረጅምና የአጭር ጊዜ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች እንዲያገኙ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በዚህም ረገድ ዩኒቨርሲቲያችን በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ ምርምር እንዲካሄድ ከፍተኛ ስራ እየሰራ ይገኛል፡፡

በተለያየ መልኩ ምርምራቸውን ለሚያሳትሙ ተመራማሪዎች ዩኒቨርሲቲው ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡ የዩኒቨርሲቲውን የምርምር ፕሮጀክቶች ተጨባጭ ሁኔታ የሚያስረዳ መጽሄትና ጆርናሎችን እያሳተመ ይገኛል፡፡

ከማህበረሰብ አገልግሎት አንጻር ዩኒቨርሲቲው በገጠርና በከተሞች የማህበረሰቡን ህይወት ለመለወጥ እየሰራ ይገኛል፡፡ የማህበረሰብ አገልግሎት የዩኒቨርሲቲው ሃብት የሆነውን እውቀት፣ ክህሎት አጠቃላይ አመለካከት ወደ ማህበረሰቡ በማስረፅ የማህበረሰብ እድገት እንዲመጣ ያስችላል፡፡ በዋናነትም የአቅም ግንባታ ሥራን ማከናወንና የማማከር አገልግሎትን ያካትታል፡፡

በባሕር ዳር ከተማ የሚሰጠው የማህበረሰብ አገልግሎት በትምህርት ዘርፍ ያሉትን አመራሮች፣ መምህራንና ተማሪዎች ያለባቸውን ክፍተት በመለየት ክፍተቱን በሚያሟላ መልኩ የአቅም ግንባታ ሥልጠና እየሰጠ ይገኛል፡፡ በተለይም በሂሳብ፣ ሳይንስና እንግሊዝኛ ቋንቋን መሠረት ያደረገ ስልጠናዎች ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ተቋም በከተማዋ ለሚገኙ አጠቃላይ የመሰናዶ ት/ቤቶች በሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርት ስልጠና ሰጥቷል፡፡ እንዲሁም ሌሎች በርካታ የስልጠና ሥራዎች በየትምህርት ቤቱ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ በቴክኖሎጂ ሽግግር ረገድ የእንጉዳይ ዘር አመራረት እና አያያዝ፣ ለስፖርት ወጌሻዎች ስልጠና፣ የሥጋና የወተት ከብቶች አያያዝ፣ የጣና ሀይቅን አጠባበቅ፣ አሳ አመራረት፣ ለታራሚዎች ስልጠና እንዲሁም ከደንገል የሚሰሩ የመገልገያ ቁሳቁስሶችን ዘመናዊነትን እንዲላበስ በማድረግ የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር እያደረገ ይገኛል፡፡

የገጠሩ ማህበረሰብ አርሶ አደር እንደ መሆኑ መጠን ዩኒቨርሲቲው የግብርናውን ዘርፍ በመደገፍ በቆለላና ብር አዳማ መንደሮች የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ፣ በዘመናዊ ዘዴ ንብ ማርባት፣ የወተት ምርትን ለማሳደግ የወተት ላሞች አመጋገብ ዘዴ፣ የዶሮና የእንቁላል ምርት ለማሳደግ የዶሮ አረባብና እንክብካቤ፣ የንፁህ ውሃ መጠጥ አቅርቦት ላይ የውሃ ጉድጓዶችን በማበልፀግ የኑሮ ማሻሻያ ሥራዎችን በመስራት የአርሶ አደሩ ኑሮ የተሻለ እንዲሆን ዩኒቨርሲቲው ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል፡፡

በቆለላ የገጠር መንደር የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ላይ ስልጠና ለመስጠትና በትምህርት ጥራት ላይ ጠንከር ያለ ሥራ ለመስራት ቡድን ተቋቁሞ እንዲጠና ለማድረግ ዝግጅት እየተደረገ ሲሆን በብር አዳማ ግን ቀደም ሲል የተቋቋመው ቡድን ባመጣው ጥናት መሰረት ለትምህርት ጥራት ማሻሻያው የሚያግዝ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በተጨማሪ የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት የሚያሳድግና የአኗኗር ዘይቤውን የሚቀይርበት የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ ተገቢ በመሆኑ ለገበሬው የተሻሻሉ ምርጥ ዘር እንዲያገኝ በአጋር ድርጅቶች ድጋፍ ሁለት የዘር አባዥ ማህበራትን በማቋቋም ለአርሶ አደሩ በማስተዋወቅ ቴክኖሎጂውን የማሸጋገር ሥራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ እንዲሁም በብር አዳማ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎችን በማሰራጨት የአካባቢውን የተፈጥሮ ሀብት ከጥፋት በመታደግ እንዲሁም የገጠሯ ሴት ጉልበቷ እንዲቆጠብ ለማድረግ ተችሏል፡፡ ጠቅላላ የመማር ማስተማሩ አመች ያልነበረውን ት/ቤት ንፅህናውን የተጠበቀ ግቢ፣ ቀለም የተቀባ እና ወለሉ የተስተካከለ በማድረግ ምቹ የመማሪያ አካባቢ እንዲፈጠር ተደርጓል፡፡

ዩኒቨርሲቲው የማህበረሰብ አገልግሎት ሞዴል የገጠር መንደሮችን በመምረጥ አርሶ አደሩ ያለውን ሀብት በመጠቀም

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

My Reflection

# Are our students delving into Research or Re-search?

**Yenus Nurie (Department of English Language and Literature)**

One of the most noticeable accomplishments of a student life is earning a university degree. There is no doubt that university has a positive impact on students' life. For example, it improves their self-confidence; prepare them to take on the harsh path that lies ahead with no fear. It is also the best place to develop their social skills. These ultimate ambitions come true after many ups and downs in the long and hard educational journey although the effort of our students pointed in the opposite direction. During their academic years, students are supposed to study hard and conduct a research for the partial fulfillment of their degree, and thereby to successfully solve immediate and long lasting research problems.

Research is not as easy as anyone assumes to be. It requires us to deeply involve ourselves in the unknown. Research is not to re-search what was revealed, but it is to reveal what was not researched. It is a complex process which demands systematic and scientific data collection and analysis. In spite of its complexity; however, effective researchers could overcome the multi-dimensional problems encircled the world.

Let all of us now imagine the motivation of our students for a moment. Do our students make their own interest to original and creative effort to the field they study, or do they make the leap from gaining theories to cheating the property of other intellectuals? Do they show genuine academic concern to what they learn in their classes, or show a lack of confidence in research? Consequently, are there fewer opportunities for our graduate students to understand the connection between the theories they amassed with the practical academic expectancies? Above all, to what end besides moving this way will go unless new checking and supervising mechanisms are utilized to control and foster their motivation to transcend their knowledge of creativity and originality to innovation and research?

Like other higher institutions, copying on senior essays from previous graduates has been a common trend among our students. It is not either difficult to see senior essays slightly copied from previous research papers, or adapted to suit their area of interest. In this case, libraries are becoming rich resources for the shameless copy and paste forgery as students are simply making use of the previous essays available.

Beginners as they are, our undergraduate students have been found to be shocked and scary to complete their study in senior essay. The majority of our students seem to lack the confidence and skills to take responsibility and believe it is up to them to conduct the research and solve the problems or at least show their practical endeavor to the theoretical lessons they studied in their fields. Others simply feel intimidated when they think of starting their research in a particular topic. Like the other members of our university instructors, I have constantly come across prospective undergraduate students who don't know where to begin even to decide a research topic which they are genuinely interested.

So as to eliminate students' dependency on the work of others and establish better research-oriented community, it is vital to address the root cause of the problem. The most important factors contributing to low quality of research papers is the little motivation of student researcher. We need to arouse the motivation and interest of our students by employing various systematic ways. We need to assist student researchers in their research, and set remedies to help them cope with the current topsy-turvy situation. Good quality studies need to generally be rewarded to create favorable and competitive opportunities among student researchers.

Equally important here is that teachers ought to be highly skeptical of the entire defense when students submit their proposal. They can reject their proposal and urge them to change, modify so that students would finally come to realize their academic dishonesty. Despite criticism from some students, this is the most important step we can do to eliminate 'mere' copying of senior essays. By the way, it is disgusting to encounter this kind of academic fraud at the expense of developing strong ambitions and dauntless visions they had to cultivate as the future hopes and dreams of generations lie on the shoulders of these graduates. In fact, no one wishes to produce intellectuals simply re-search what is obvious, for they are unable to contribute little to the society they come from.

It is a common misunderstanding that undergraduate researchers can be successful only on their own independent approach, hard work, and dedication. Equally important; however, is the contributions of the advisor in the student-mentor relationship. The good rapport established between the advisee and advisor is the key to success. In the first place, I soon discovered that some advisors did not feel the same way as experts in the field advocate. For example, during the semester that students were doing their research, I observed s only some advisors who scheduled regular meetings with their undergraduate researchers to monitor and assist their advisees' progress. It was also apparent to see energetic and enthusiastic advisors who were passionately supervising their students. On the contrary, it was surprising to have student researchers with little or no devotion and loyalty on the part of their research.

Indeed, I know how difficult it can be to put this misbehavior to an end, and respond to large scale incidents of the current academic dishonesty, yet it does not seem to be fair and suffice either to condemn students for their wrong deeds. On the other hand, if left unchecked, it is not difficult to guess the damaging consequences of students' shameless copying, which the subsequent generations will also expect of each other.

The university needs to set up special research units that ensure quality, monitor progresses and supervise and assist undergraduate students in supplementing research trainings besides the courses they take in each college, faculty or school, and therefore, fostering our students by establishing special unit is the foundation for a successful career in research in our undergraduate programs. Each faculty, college or school mentors should help students who are still hesitant on starting their research. For example they can train undergraduate students about how to explore and discover a topic of interest in their fields of study.

# የግጥም ጥግ

## አንዳንድ ሰው……

«ተምረሃል ….. ?» ሲሉት ያሳያል ፎቶውን፣
ከቤት ግድግድ ላይ ያጠለጠለውን፣
……………………. የጥቁር ጋወኑን፡፡
«ታገባለህ….?» ሲሉት «እንዴታ!» ነው መልሱ፣
ያልሆነውን ሊሆን ይኮፈሳል እርሱ፡፡
«ትፅፋለህ….?» ሲሉት «አለኝ!» ይላል ድርሰት፣
ሕዝብ ያላነበበው ባሳታሚ እጦት፡፡
እርሱ ይበል እንጂ እውነታው ሲጣራ፣
እንኳን ሲፅፍ ቀርቶ የተባፈ አላየም የፊደል አዝመራ፡፡
አውቀን ከታዘብነው ሁሉን በጥሞና፣
ሞልቷል በየቤቱ ጉራ ያሳበጠው ባዶ ገረወይና፡፡
…………. ይሰውረን ……………….

## ብዙዎች ቢነሱ

ተቀምጠው የሚውሉ ተኝተው ‘ሚያነጉ፣
ብዙ እኛዎች  አሉ ለእኛ የማይበጁ ለእኛ የማይተጉ፡፡
ጥቂቶች እኤዎች እኛን የዘነጉ እኤን የሚወዱ፣
በስግብግብ መንፈስ ከፍ ብለው ቢታዩ ርቀው ቢሄዱ፡፡
አይፈጥርም ሀሴትን ልቦናም አይረካ፣
የጥቂቶች ስኬት እንደ ሀገር ሲለካ፡፡
ሀገር የምትቀናው እድገት የሚመጣው፣
ብዙዎች ተነስተው … ጥቂቶችን አልፈው፣
ብዙ እኛዎቹ ለእኛ …. ሲፈጉና ለእኛ ሲተጉ ነው፡፡

## እንቅፋት

በራዕይ ጉዳና ደፋ ቀና ሲሉ፣
በስኬት ማማ ላይ በመውጣት ላይ ሳሉ፡፡
መውጣት የተሳነው ወኔው የመከነ፣
በተንኮል ለመኖር ልቡ የጀገነ፡፡
ብዙ አለ ጋሬጣ ማሰብ የተሳነው፣
እንቅፋት … ሰው ለሰው…፡፡

ደስታ ተከስተ (BDU Security Service)

## እብድና ድሃ

ዕብድን ዕብድ ያሰኘው፣
በባዶ እንጀቱ በዕርቃን ስጋው፣
በጠራራ ፀሃይ በዛ በሚሞቀው፣
የጎዳውን ጎድቶ ዝም ብሎ ሲሄድ ነው፣
ለምን ይህን አደረክ? የሚል ጠያቂ ሰው፣
ደፍሮ ‘ሚጠጋው የለ! እንኳንስ ‘ሚከሰው፡፡
ደሃም ከቀረጠ ከዕብድ እንኳ ይከፋል፣
አምርሮ የወጣ ቀን ዕብዱ ሰው ይሻላል፡፡

ድሃ ተስፋ ሲቆርጥ፣
ክፉ ደጉን ሳይመርጥ፣
በዕኩለ ሌሊት ቤተክርስቲያን ሄዶ፣
መቃብርን ንዶ፣
በድን አውጥቶ ነው መልሶ ‘ሚገለው፣
ሁለተኛ ሞትን ደግሞ ‘ሚለግሰው፡፡

ከፍሬዘር ታሪኩ የእመቤት ልጅ
(አፍላጋት)

## ውድ የናይል ጋዜጣ አንባብያን

የናይል ግንቦት ወር እትም ላይ ‘ዩኒቨርሲቲው ለፕሮፌሰር ሙሉጌታ ክብረት የእንኳን ደስ ያለዎት መርሀ ግብር አዘጋጀ’ በሚለው ዜና ላይ ‘የህይወት ታሪክ’ ሳይሆን ‘የህይወት ተሞክሮ’ ሆኖ እንዲስተካከል እንዲሁም በሰኔ ልዩ እትማችን ዩኒቨርሲቲው የመሬት አስተዳደር ተቋምን የከፈተው ከኔዘርላንድ መንግስት ጋር ሳይሆን ከስዊድን መንግስት ጋር በመተባበር እንደሆነ እየገለጽን ለተፈጠረው ስህተት ውድ አንባቢዎቻችንን ይቅርታ እንጠይቃለን፡፡

ዝግጅት ክፍሉ

# ባሕል

# “ጨኅራ ለበሰ”

በአደላች ታፈረ

የርቀት ትምህርት ተማሪ (እንጅባራ)

ኢትዮጵያ የብዙ ብሄር ብሔረሰቦችና ቱባ ባሕሎች ባለቤት መሆኗ ይታወቃል፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ ብሄር ብሔረሰብ ደግሞ የየራሱ የሆነ የአመጋገብ፣ የአለባበስ፣ የቋንቋ አጠቃቀምና የራሱ አኗኗር ዘይቤ አለው፡፡ ከእነዚህም አንዱ በአማራ ክልል (በምዕራብ ጐጃምና በአዊ አስተዳደር ዞኖች) በሚገኙ አንዳንድ ወረዳዎች የገጠር መንደሮች ውስጥ “እያ እገሌ ጨኅራ ለበሰ” የሚሉ አፈ ታሪኮች ይሰማሉ፡፡

ለመሆኑ ጨኅራ ለበስ ማለት ምን ማለት ነው? እንዴትና ለምንስ የላበሳል? የሚሉ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ፡፡ ነገሩ ወዲህ ነው፡- አብዛኛው የአካባቢው ገበሬዎች በጥምር ግብርና የሚተዳደሩ ሲሆን የከብት ቁጥር መጨመርና መንጋ መለየት እንደታላቅ፣ ታታሪና ሀብታም ገበሬ ስለሚያስብል የከብቶችን ቁጥር ማብዛት ትኩረት የሚሰጠው ተግባር ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ይመስላል በተለይም ሃምሳና በላይ ጥገቶች (የወተት ላሞች) ሲኖራቸው ቤተዘመድ፣ ጎረቤት፣ የሀገር ሽማግሌዎች ተገኝተው እንደተዋረዳቸው በታደሙበት ሀብታሙ አባወራ ከመንጋው መሀል አንድ በሬ መርጦ ያርዳል፡፡ ከዚያም የበሬው ጨኅራ ፈርሱን በማራገፍ ሳይታጠብ አባወራው በዘወትር ልብሱ ላይ እንደካባ ደርቦ ይቀመጣል፣ ባለቤቱም የክት ልብሷን ለብሳ በክብር ትቀመጣለች፡፡ የሁሉም ላሞች ወተት ታልቦ በጋን ይጠራቀምና እየተቀዳ በጥሬው እየተጠጣ፣ ስጋ እየተበላ፣ እንደአስፈላጊነቱ ጉዝጉዞ (የቅቤና የአዋዜ አብዚ) ጠላ፣ ጠጅ ቀርቦ ፌስታ ሲሆን ከዋለ በኋላ ድሀ ዘመዶች፣ የቅርብ ባለሟሎች ባለሀብቱን በጉልበት ለብዙ ጊዜ ያገለገሉና ለሀብት ክምችት አስተዋጽኦ ያበረከቱ ግለሰቦች የከብት ስጦታ ተደርጐላቸው ከተመረቀ በኋላ ተላብሶ የዋለው ጨኅራ ጉድኅድ ተቆፍሮ ይቀበርና የዕለቱ ዝግጅት ሲጠናቀቅ ባለሀብቱ በአንት ወይም በወተት ታጥቦ ቤቱ ይገባና የክት ልብሱን (ጃኖ) ይለብሳል፡፡ ከዚህ ቀን ጀምሮ ግለሰቡ ታዋቂነትን የሚያገኝበት፣ ዝናን የሚያተርፍበት፣ ለደጅአዝማችነት፣ ለቀኝ አዝማችነት የሚታጭበትና ነጋዴም ከሆነ ነጋድራስ የሚል ሹመት የሚያገኝበት ነው፡፡ እንዲሁም ከዚያ በፊት የአርበኝነት ጀብዱ የፈፀመ ከሆነ ወይም አዳኝ ከነበረ ባለቤቱ በሄደችበት ቦታ ሁሉ ክብርና ቅድሚያ መስተንግዶ ታገኛለች፡፡ ለምሳሌ ውሃ ለመቅዳት፣ በግብዣና ማህበር ቤቶች መጀመሪያ እጅ የመታጠብ፣ ዋንጫ የመቀበልና ጠላ የማስቀዳት የመናገር መብቶች ሁሉ መጀመሪያ የእሷ ነው፡፡

ሌላው ደግሞ በዚሁ ቀበሌ ሌላ ሀብታም ይኸን ሲያደርግ ወይም ከእሱ በኋላ ጨኅራ ሲለብስ በአንድ ጥገና እየበለጠ መሄድ የተለመደ ተግባር እንደነበረ የዓይን ምስክሮች ይገልፁታል፡፡ ይኸም የሚያሳየው ሪከርድ እንደማሻሻል ሳይቆጠር አይቀርም የሚል ግምት አለኝ፡፡

በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች (ዝብስት፣ ቁንዝላ፣ አቸፈር….) ያለው አካዋወን ትንሽ ለየት ያለ ነው፡፡ ይኸውም በዕለቱ የላሞች ወተት ታልቦ በገንዳ ከተሞላ በኋላ ባለሀብቱ ገብቶ ይታጠብበታል (ይዋኝበታል) ያንን ከብቶችና ውሾች ይጠጡታል፡፡ በሬ ታርዶ ይበላል ይጠጣል፣ ነገር ግን ጨኅራው በአካል አይለበስም፡፡

በሀብትነት የሚቆጠሩ እንስሳትም ቅዱስ የሚባሉ ከብቶች ብቻ (ማለትም የቀንድ ከብቶች ብቻ) መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡

ምንጭ፡- - አቶ አለማየሁ ተስፋዬ (ከትሊሊ)እና

መምህር ጌትነት አድምጥ (ከዳንግላ)

# እኛ እንዲህ እንላለን ...

ከገጽ 7 የዞረ

ሁሉ መሆን አለበት፡፡ ይህም ተማሪዎች በርካታ አማራጭ የምርምር ዘዴዎችን በሚገባ አውቀው እነሱ ለሚሰሩት ምርምር ይበልጥ ተመራጭ የሆነውን እንዲጠቀሙ ይረዳቸዋል፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተጠቅመን ተማሪዎቻችን የምርምር እውቀት ብቻ ሳይሆን የምርምር ፍቅርም እንዲያድርባቸው መጣር ይጠበቅብናል፡፡ 2ኛ) ማማከር ትልቅ ኃላፊነት እንደሆነ ተገንዝበን አቅም በፈቀደ መጠን ለተማሪዎች የምርምር ስራ ተገቢ እገዛና ክትትል ማድረግ፤ ለተማሪዎች ያለባቸውን ኃላፊነት በግልጽ መንገር/ማስታወስ፡፡ 3ኛ) ማንኛውም ሰው ለሰራበት ብቻ እንደሚከፈለው አውቀን ለማንሰራው ስራ ክፍያ ከመጠየቅ መቆጠብ፤ ይህም የምናማክራቸው ተማሪዎች ቁጥር ከምንችለው በላይ እንዳይሆን የሞራል ግዴታ ውስጥ ያስገባናል፤ የመማርና የማስተዋል መገለጫም ነውና፡፡ 4ኛ) ተማሪው እያቀረበው ያለው ስራ የሰው ስላመሆኑ ለማወቅ የሚያስችሉንን ዘዴዎች (ቴክኖሎጂዎች) አቅም በፈቀደ መጠን መጠቀም፡፡ 5ኛ) የሰውን ስራ ወይም ሃሳብ እንደ ራስ ወጥ ስራ አድርጎ ያቀረበ ተማሪ ላይ አስተማሪ የሆነ ቅጣት መውሰድ (አንድ ዓመት መጨመሩ ፌዝ ነው ብለን እናምናለን)፡፡

## 2. ተገቢ የሆነ የማማከር አገልግሎት አለመስጠት

ሙያዊ የማማከር አገልግሎት መስጠት የዩኒቨርሲቲው አንድ ትልቅ ስራ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎችን ከማማከር ይጀምራል ብንል የተሳሳትን አይመስለንም፡፡ ከላይ እንደጠቀስነው ተማሪዎች ለስራቸው ከማንም በላይ ኃላፊነት ሊወስዱ ይገባል፡፡ ይህ ግን አማካሪው በየትኛውም መመዘኛ ንጹህ ነው ብሎ ደፍሮ ለመናገር አያስችለንም፡፡ ምክንያቱም ከአንዳንድ ተማሪዎች የመመረቂያ ጽሁፍ እንዲሁም በተቋቁሞ (defense) ወቅት እንዳየነው አንዳንድ መምህራን ተገቢ የሆነ የማማከር አገልግሎት አይሰጡም ወይም ኃላፊነታቸውን አይወጡም፡፡ ለምሳሌ አንድ ተማሪ በባሕር ዳር ከተማ የሚኖሩ የሲዳማ ብሔረሰብ አባላት ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ስላላቸው ግንኙነት (intergroup relation) ያጠናል፤ ከመረጃ ምንጮች መካከል በባሕር ዳር ከተማ የሚኖሩ የሲዳማ ብሔረሰብ አባላት እንደሆኑም ይገልጻል፤ የጥናቱን ውጤት ሲያቀርብ በባሕር ዳር ከተማ የሚኖር አንድም የሲዳማ ብሔረሰብ አባል የለም ይላል፡፡ ይህን ስናይ ተማሪው አብዷል ልንል እንችላለን፡፡ ይህንን የጥናት ስራ ያማከረውን (ካማከረ ማለታችን ነው) መምህርስ ምን እንበል?

ሌላው የማማከር ስራ ድክመት መገለጫ የሚሆነው አንድ አማካሪ በተመሳሳይ ርዕስ ብቻ ሳይሆን እርስበእርስ የተገለባበጡ የድህረ ምረቃ መመረቂያ ጽሁፎችን በተለያዩ ዓመታት አማከርኩ ብሎ ለተቋቁሞ እንዲቀርቡና እንዲመረቁ ማድረጉ ነው፡፡ ለዚህ አስረጅ የሚሆኑ መመረቂያ ጽሁፎችን በቤተመጻህፍታችን ማግኘት ቀላል ነው፡፡

በዩኒቨርሲቲያችን አንዳንድ ተማሪዎችም ለድክመታቸውና ለስራቸው ብልሹነት አማካሪዎችን ሲወቅሱ ይደመጣል፡፡ ይህ የተማሪ የተለመደ ወይም ደካማ ባህርይ ነው ልንል እንችላለን፡፡ ከተቋቁሞ በኋላ የቅርብ ዘመዱን እንዳረዱት ሰው እንባውን እያወረደ "አማካሪዬ አንድ ጊዜ ብቻ ነው ያየልኝ፤ በተደጋጋሚ እንዲያይልኝ ብጠይቀውም ‹ቢዚ ነኝ› ስራና መጨረሻ ላይ አይልሃለው ነው ያለኝ" ያለንን ግን ዝም ብለን አናልፍም፡፡ የምርምር ስራውን የሚሰራው ተማሪው ቢሆንም አማካሪውም የመከታተልና የማገዝ ኃላፊነቱን በሚገባ ሊወጣ ይገባል፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን "የተማሪ የተለመደ ወይም ደካማ ባህርይ ነው" ብሎ ማለፍ ተገቢም ፍትሃዊም ነው ብለን አናምንም፡፡ በአጠቃላይ ተገቢ የማማከር አገልግሎት አለመስጠት ሌላው የአካዳሚያዊ ኢታማኝነት (academic dishonesty) መገለጫ ነው፡፡

ተገቢ የማማከር አገልግሎት ላለመስጠት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉት ምን ምን ናቸው? በተወሰኑ ከሌጆች/ፋኩልቲዎች/ትምህርት ክፍሎች መምህራን በመደበኛና በክረምት መርሃ ግብሮች በርካታ ተማሪዎችን ሲያማክሩ ይስተዋላል፡፡ ይህም ከማስተማር፣ ከማህበረሰብ አገልግሎትና ከሌሎች ኃላፊነቶች በተጨማሪ የሚሆንበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ በቂ ጊዜ መድበው ተማሪዎቻቸውን ማማከርና መከታተል ሲያዳግታቸውም ወይም እንደነገሩ ሲያዳርሷቸው ይስተዋላል፡፡ አንዳንድ መምህራን እስከ 18 የሚደርስ የድህረ ምረቃ መመረቂያ ጽሁፎችን ሲያማክሩ ይስተዋላል፡፡ ይህ የሆነው በግድ ወይም ለፕሮግራሙ አስበን ነው ሲሉም ይደመጣል፡፡ ይህ ግን በፍጹም ተቀባይነት የለውም፡፡ ቢሆንም እንኳን ፕሮግራሙን የሚያዳክም አይነተኛ መሳሪያ ስለሆነ አንድ ሊባል ይገባል እንላለን፡፡

እና ምን እናድርግ? ማንም ሰው ለሚያበረክተው አስተዋጽኦ በመመሪያ መሰረት የተቀመጠለትን ጥቅም የማግኘት መብት አለው፡፡ ነገር ግን በየትኛውም መስፈርት የማማከር ስራ የሚያስገኘው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ቀዳሚ ሆኖ ሊታይና ዋነኛ የመከራከሪያ ነጥብ ሆኖ ሊቀርብ አይገባውም፡፡ መምህራን ብዙ ተማሪዎችን የሚያማክሩት ተገደው ከሆነ አስገዳጁ አካል አንድ ሊባል ይገባል፡፡ ወደው ከሆነ ግን ከገንዘብ ይልቅ ኃላፊነትና ሙያዊ ክብር ይቅደም እንላለን፡፡ ለዚህም በተለያዩ ዕርከኖች ላይ የሚሰሩ ኃላፊዎች (ከትምህርት ክፍል ተጠሪ እስከ ፕሬዚደንት) አርአያ ሊሆኑ ይገባል፤ ለበጎም ሆነ ለእኩይ ዓላማ ከላይ የፈሰሰ ውሃ ታች መድረሱ አይቀርምና፡፡ ለአንድ መምህር የማማከር ስራ የሙያና የሞራል ግዴታ ነው፡፡ ስለሆነም ሙያዊ ክብርን ለመጠበቅና የሞራል ግዴታን ለመወጣት ስንል የሌላ ኃይል ጉትጎታና ክትትል ሳያስፈልገን ተማሪዎቻችን በአግባቡ እናማክር እንላለን፡፡

## 3. የመመረቂያ ጽሁፎችን ተቋቁሞ (defense) በተገቢው መንገድ አለማከናወን

በአንዳንድ ፋኩልቲዎች/ኮሌጆች ለመመረቂያ ጽሁፎች ግምገማ ሂደት የተሰጠው ትኩረት የሚያሳዝን ነው፡፡ ከዚህ የተረዳነው በዩኒቨርሲቲያችን ውስጥ ተቋቁሞ ምንድን ነው? ለምን አስፈለገ? በተቋቁሞ ወቅት የትኞቹ አካላት የግድ ይገኙ? ተቋቁሞው እንዴት ይከናወን የሚሉ ጥያቄዎች እንዲነሱና የሚመለከተው አካል መልስ እንዲሰጥባቸው ግድ ማለቱን ነው፡፡ ለዚህ ማሳያ ከሚሆኑት መካከል ለፈታኞች በቂ የማንበቢያ ጊዜ አለመስጠት፣ ተቋቁሞውን በአጭር (በቂ ባልሆነ) ጊዜ አጣድፎ መጨረስና የአማካሪዎች ሚና በግልጽ አለመታወቅ ይገኙበታል፡፡ ስለአጠቃላይ ጉዳዩ እንዲህ ካልን ስለፈታኝ መምህራን ደግሞ እንዲህ እንላለን፡፡

አንዳንድ መምህራን የመመረቂያ ጽሁፍን መገምገም የሚፈልጉበት ብቸኛ (ዋነኛ አላልንም) አላማ ለዚያ ስራ የተመደበውን ክፍያ ለማግኘት ሲሆን አስተውለናል፡፡ እነዚህ መምህራን የተማሪውን የመመረቂያ ጽሁፍ ምንም ሳያነቡ የሚመጡና ተማሪው ከሚያቀርበው ወይም ተማሪው በሚያቀርብበት ወቅት የመመረቂያ ጽሁፉን ገለጥ ገለጥ አድርገው ከሚያዩት ወይም ከሌላኛው ፈታኝ ሃሳብ በመውሰድ ጥያቄ የሚጠይቁ (ፈታኝ ሳይሆኑ ተጋባዥ ጠያቂዎች) ናቸው፡፡ ይህ አካዳሚያዊ ኢታማኝነት (academic dishonesty) ነው፡፡ እንዲህ አይነቱ ስራ የሚሰራው በሙያቸው ረዳት ፕሮፌሰርና ከዚያም በላይ ብሎም የተለያየ ኃላፊነት ባላቸውና ለሌሎች መምህራን አርዓያ ይሆናሉ ተብሎ በሚታሰቡ ሰዎች ሲሆን ችግሩ የጎላ እንደሚሆን ግልጽ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ የቀረበው ስራ ሙሉ ለሙሉ የተማሪው እንዳልሆነ እያወቁ፣ ‹‹ተማሪው ቢደግምም ከዚህ የተሻለ አይሰራም፤ በሌሎች ትምህርቶች ጎበዝ ነው፤ አማካሪው ቅር ይለዋል›› እና ሌሎችንም ተራ ምክንያቶች በመደርደር የማለፊያ ውጤት የሚሰጡ ፈታኞችም አሉ፡፡ ይህም አካዳሚያዊ የሞራል ዝቅጠትና እወደድ ባይነት ያሸነፈው ህሊና ውጤት የሆነ የአካዳሚያዊ ኢታማኝነት (academic dishonesty) መገለጫ ነው፡፡

አንዳንድ ፈታኝና አማካሪዎች ደግሞ ተማሪው ያቀረበው ስራ የplagiarism ውጤት እንደሆነ በማስረጃ ቀርቦላቸው እያለ ሌላኛው ፈታኝ ውጤት እንዲሰጥ ለማግባባትና ለመለመን የሚያደርጉት ጥረት አካዳሚያዊ ኢታማኝነት (academic dishonesty) በመምህራን ዘንድ ምን ያህል ስር እየሰደደ እንደሆነ ማሳያ ነው፡፡ እነዚህ መምህራን አልፎ ተርፎ እኔ እኮ ‹‹ውጤት ልሰጥህ ነበር እሱ ነው እንጂ የጠመመው፣ እሱ ነው እንጂ እንዲህ ያለው፣ እሱ ነው እንጂ...›› በማለት አውቀውም ይሁን ሳያውቁ በተማሪዎችና በፈታኝ መካከል ቁርሾ/ጠብ እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናሉ፡፡ በዚህ የተነሳ ስራቸውን በአግባቡ የተወጡ መምህራን በተማሪዎች ማንጓጠጥ፣ ማስፋራራትና ዛቻ ሲደርስባቸውና ሲሸማቀቁ፣ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት ያቃታቸውና እወድድ ባዮች ግን ህሊናቸውን ሸጠው እንደልባቸው ይንቀሳቀሳሉ፤ በተማሪዎች ዘንድ እሱ/እሷ ፈታኝ ሆኖ/ሆና በደረሰችኝ ይባላሉ፡፡ ይህ ውርደት እንጂ ክብር እንዳልሆነ ግን አይረዱትም፤ የዩኒቨርሲቲውም ማሕበረሰብና አሰራርም ስራቸውን አያወግዝም፡፡ እኛ ግን ውጉዝ ብለናል፡፡

ለዚህ ምክንያቱ ምንድን ነው? ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ለዚህ ዋነኛው ምክንያት ለመመረቂያ ጽሁፍ ተቋቁሞ በሚመለከታቸው ክፍሎችና በመምህራን የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ መሆን ነው፡፡ ሌላኛው ምክንያት ኃላፊነትን ሳይወጡ ጥቅም ለማግኘት የሚሞክሩና በስማቸው የሚነግዱ መምህራን መፈጠር፣ ማደግና እነዚህ ለይቶና ደፍሮ አንድ የሚል አካል መጥፋቱ ነው፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪ ሙያዊ ግዴታና ክብርን በእወደድ ባይነት የሚለውጥ አካዳሚያዊ ትውልድ መፈጠሩና ይህም አለመወገዙ ሌላ ምክንያት ነው፡፡

እና ምን እናድርግ? በቅድሚያ መምህራን ሙያችንን እናክብር፡፡ የሙያ ጓዶቻችንን ያልተገባ ተወዳጅነት ለማትረፍ ብለን አሳልፈን አንስጥ፡፡ ሙያውን በአግባቡ የሚወጣን መምህር ከማጣጣልና ነገር አራጋቢ አድርጎ ከመውሰድ እንቆጠብ፤ ይህ ለመልካም ስራ ሽልማት ሊሆን አይችልምና፡፡ በስራችን እንጂ በስማችን ለመታወቅና ለመኖር እንሞክር፡፡ ድክመትን የሚያለባብስና የሰጠነውን ያልተገባ አደራ የሚወጣ እበላ ባይ ፈታኝ ለማምጣት አናስብ፡፡ የሚመለከተው ክፍልም የተቋቁሞ ስርዓትን በተመለከተ መመሪያ ቢያወጣና ለተገቢነቱም አስፈላጊውን ክትትል ቢያደርግ መልካም ነው እንላለን፡፡

## 4. የተለያዩ የታተሙ/ያልታተሙ የምርምር ውጤቶችን ከንባብ መደበቅ

በመግቢያችን ላይ እንደጠቀስነው ዩኒቨርሲቲያችን የመመራመር ባህል እንዲጎለብት ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ እንዲህ አይነት ጥረት ከመምህራን ቅን አስተሳሰብና ጉልህ አስተዋጽኦ ውጭ እንኳንስ ግቡን ሊመታ ሊታሰብም አይችልም፡፡ ይህም መምህራን በመመራመር በኩል ምን ያህል ድርሻና ኃላፊነት እንዳለባቸው ያሳያል፡፡ ይህንን ከፍተኛ ኃላፊነት ለመወጣት መምህራን የምርምር ውጤታቸውን ለመማር ማስተማር አገልግሎት ማዋል፣ በተለያዩ አካዳሚያዊ ስብሰባዎች (ኮንፍረንሶች) ማቅረብና መወያየት እንዲሁም ቢያንስ ለዩኒቨርሲቲው ማሕበረሰብ ፍጆታ እንዲውሉ የተቻላቸውን ሁሉ ማድረግ አለባቸው ብለን እናምናለን፡፡ ይሁን እንጅ አንዳንድ መምህራን ይሄን ያህል የምርምር ስራዎች አሳተምኩ ሲሉ፣ አንዳንዶቹም በምርምር ስራቸው ሲያድጉና ሲሸለሙ ሰምተናል፤ አይተናል፡፡ ከነዚህ መምህራን መካከል የተወሰኑት ያሳተሟቸውንም ሆነ

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

# እኛ እንዲህ እንላለን ...

ከገጽ 13 የዞረ

በተለያዩ ቦታዎች ያቀረቧቸውን ስራዎች ለተማሪዎቻቸው፣ ለስራ ባልደረቦቻቸው እንዲሁም ማንበብ ለሚፈልጉ ሰዎች ሲያካፍሉ ወይም በቀላሉ እንዲገኙ ሲያደርጉ እንዲሁም ሲጠየቁ ለመስጠት ፍቃደኛ ሲሆኑ አይስተዋልም፡፡ እዚህ ጋር ይህ ለምን ሆነ ብለን እንጠይቃለን፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ለማስተርስና ለፒኤችዲ ዲግሪ ማሟያ የሰሯቸውን ጥናቶች ለአንባቢያን ተደራሽ ይሁኑ የሚል ሃሳብ ሲቀርብ ለምን ብለው ሽንጣቸውን ገትረው ይከራከራሉ፡፡ እኛም ለምን አይሆንም ብለን እንሞግታለን፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ለአንባቢ እንዳይደርሱ ዘብ የሚቆምላቸው አካዳሚያዊ ስራዎች ምን ቢሆኑ ነው ብለን ደግመን እንጠይቃለን፡፡ የመመራመር አላማውስ ምንድን ነው? የምርምር ውጤቱን ለአንባቢያን ማቅረብና ከተቻለም ለውጤቱ ተግባራዊነት አስተዋጽኦ ለማድረግ መንቀሳቀስ አይደለምን?! የምርምር ውጤት በተለያየ መልኩ ለአንባቢ እንዳይደርስ ማድረግስ የአካዳሚያዊ ኢታማኝነት (academic dishonesty) መገለጫ አይደለምን?

ይህ ለምን ሆነ? ለዚህ ትክክለኛውን ምክንያት የሚነግሩን የመሰል ተግባራት ተዋንያን ናቸው፡፡ እኛ ግን አንድም በስራቸው አይተማመኑም፤ አንድም ሙያዊ ትችትን ይፈራሉ፤ አንድም የምርምሩ አላማ (ምርምር ከተባለ) እድገትና ሽልማት ማስገኘት እንጂ ሌላ ስላልሆነ ሊሆን ይችላል እንላለን፡፡

እና ምን እናድርግ? ለዚህ መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ በርካታ አማራጮች ሊኖሩ ቢችሉም እኛ ግን ማንኛውም እድገትም ሆነ ሽልማት የሚጠየቅበት የምርምር ስራ በሚመለከተው የዩኒቨርሲቲ ቤተመጻህፍት እንዲቀመጥና ለንባብ ፍጆታ እንዲበቃ መደረግ አለበት እንላለን፡፡ ይህን የማይፈልግ ማደግም መሸለምም የለበትም ብለንም እናስባለን፡፡ መምህራንም ለአደባባይ የማይበቃ ስራ ከማሳተም እንቆጠብ፡፡ የምርምር ስራ እየሰራን ሳለንም ሆነ ካሳተምን በኋላ በጓደኞቻችን የሚሰጡንን ገንቢ አስተያየቶች በቅን ልቦና የማየትና የመቀበል ባህል እናዳብር፡፡ ከእውነተኛ ተመራማሪ የሚጠበቀው ይህ ነውና፡፡

ስለ አካዳሚያዊ ኢታማኝነት እኛ ካለፍንበት፣ ካየነውና ከሰማነው ይህን ብለናል፡፡ ነገር ግን በዩኒቨርሲቲያችን ያሉት የአካዳሚያዊ ኢታማኝነት መገለጫዎች እነዚህ ብቻ ናቸው ማለት አይደለም፡፡ እኛ እንዲህ ስንል የታዘቡ፣ ውስጣቸው የተነካ፣ ቅን አሳቢና ተቆርቋሪ መምህራንና ተማሪዎች እንዲያ ብለው፣ አስረጅ አቅርበው የበለጠ የመማሪያና የመተራረሚያ ሃሳብ ያመጣሉ ብለን በማሰብ እንጂ፡፡

## እንደ ማጠቃለያ

ዩኒቨርሲቲያችን በምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲነት እንዲታወቅ ጥረት ስናደርግ ስራችንን ከሚያጎድፉ ተግባራት መጠንቀቅ ለነገ የሚባል ስራ አይደለም ፡፡ ከነዚህ መካከል አካዳሚያዊ ኢታማኝነትን አጥብቆ መታገል አንዱ ሊሆን ይገባል እንላለን፡፡ ይህን በተመለከተ አዲሱ የዩኒቨርሲቲው መተዳደሪያ ደንብ (legislation) መሰል ጉዳዮችን ሾላ በድፍን ብሎ ሊያልፍ አይገባውም፡፡ የምረቃ ጽሁፍን (ፕሮጀክትን) እና ማማከርን በተመለከተ ራሱን የቻለ ግልጽ መምሪያ (guideline) ሊኖር ይገባል፡፡ ይህ መምሪያ ከአንድ ተመካሪና አማካሪ ምን ምን እንደሚጠበቅ፣ የተመካሪ መብትና ግዴታን፣ የአማካሪ መብትና ግዴታን እንዲሁም በሁለቱ መካከል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት በዝርዝርና በግልጽ የሚያስቀምጥ መሆን አለበት፡፡ መምሪያው የማማከር ሂደቶች ምን መምሰል እንዳለባቸው ሊያትት ይገባል፤ ስርቆትን በተመለከተ የዩኒቨርሲቲው መተዳደሪያ ደንብ አጽንኦት ሰጥቶ እንዲያትት ማድረግና መምሪያውም ይህን ጠቅሶ ስለስርቆት አይነቶችና ቅጣት በዝርዝር ሊያስቀምጥ ይገባዋል፡፡ እዚህ ላይ የሌሎች ተቋማትንና ሀገሮችን ተሞክሮ ማየቱ ጠቃሚና የእርምጃውን አስተማሪነት ያጠናክራል የሚል እምነት አለን፡፡ ይህ መምሪያ እነዚህን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ተመሳሳይ ጉዳዮች የሚያቀርብ መሆን መቻል አለበት፡፡ ለምሳሌ፣ ተማሪው የመመረቂያ ጽሁፉን ከተቋቋሞ በፊት ስንት ቀን ቀድሞ ያስረክብ? ፈታኞች ለማንበብ ስንት ቀን ይሰጣቸው? ፈታኞች እንዴት ይመረጡ? የፈተናው ሂደት ምን ይምሰል? እነማን የመገኘት ግዴታ አለባቸው? ተቋቁሞውን ማን ይምራው? የውጤት አሰጣጡ ምን ይምሰል (የውስጥ ገምጋሚ፣ የውጭ ገምጋሚ)? የተሰጠው ውጤት የሚያሳልፍ ከሆነ ተማሪው የተሰጠውን አስተያየት አካቶ በስንት ቀን ውስጥ ያስረክብ? ስንት ጥራዝ? ሶፍት ኮፒ ያስፈልጋል? ለማን ያስረክብ? ተማሪው በተሰጠው ውጤት የማይስማማ ከሆነ ቅሬታውን እንዴት ያቅርብ? ፈታኞችን ወይም አማካሪውን ቢያንገራግር፣ ቢያስፈራራ ምን መደረግ አለበት? ወዘተ የሚሉት ሊካተቱ ይገባል፡፡

አንድ መምህር በድህረ ምረቃ ደረጃ ቢበዛ ስንት የማስተርስና ስንት የፒኤችዲ ዲግሪ ተማሪ ማማከር እንደሚችል በግልጽ መታወቅ አለበት፡፡ ይህም መምህራን ያለባቸውን ኃላፊነት እንዲሁም የትምህርት መርሃ ግብሮችን (መደበኛ፣ የክረምት፣ የርቀትና የተከታታይ) ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡ አለበለዚያ ነገሩ ብዙ ልጅ በተከታታይ ሲወልድ ለምን እንዲህ ትወልዳለህ አራርቀህ መውለድ አለብህ ሲሉት፣ አንዱን ባህር ዳር፣ አንዱን አዲስ አበባ፣ አንዱን ሐዋሳ፣ አንዱን ድሬደዋ… በማድረግ አራርቄ ወለድኩ እንዳለው ሰውዬ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም ማለት አንድ መምህር በአንድ የትምህርት ዘመን በየትኛውም መርሃ ግብር በሚሰጡ የድህረ-ምረቃ ፕሮግራሞች ላይ የሚሰጠውን የማማከር ስራ ጫና ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡

በስተመጨረሻም በየትኛውም አይነት አካዳሚያዊ ኢታማኝነት መዘፈቅ አስነዋሪ ነው፡፡ እንዳላዩ ማለፍም ‹‹አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ›› ስለሚሆንብን ከወዲሁ እንታገለው፡፡ በተጨማሪም አካዳሚያዊ ኢታማኝነት የተለመደ ነው፣ ምን እናድርግ፣ ከአቅማችን በላይ ሆኖ እኮ ነው፣ ሃይ የሚል ጠፋ ከማለት ይልቅ ለምንሰራው ስራና ለቆምንለት ዓላማ ጋሬጣ ስለሆነ በየትኛውም መንገድ ሳንደክም ልንታገለው ይገባናል፡፡ ለዚህም የዩኒቨርሲቲው ድጋፍም ይለየናል ብለን አናስብም፡፡ ቸር እንክረም!

# የዩኒቨርሲቲው የ2007...

ከገጽ 10 የዞረ

አካባቢውን የተሻለ የመኖሪያ ቦታ እንዲፈጥር ለማደረግ ሞዴል የገጠር ቤቶችን የመገንባት ስራ እየሰራ ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲው እነዚህን ሞዴል የገጠር መንደሮች ተሞክሮ ወደ ሌሎች የክልሉና የሀገሪቱ አካባቢዎች እንዲስፋፉ በማድረግ ለገጠር ልማት አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ እየጠፋ የነበረውን የጣና እና ዓባይ ዙሪያ ተክል የሆነው ደንገል በተለያዩ ውሃማ በሆኑ አካባቢዎች በመትከል እንደገና የደንገል ልማት እንዲስፋፋ የማድረግ ስራ ሌላው ዩኒቨርሲቲው ትኩረት የሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ በተለይ በፔዳ ዋናው ግቢ በሚያልፈው የቆሻሻ ፍሳሽ ቦይ ዳር ለዳር የተተተከለው ደንገል ለእይታ አስደሳች ከመሆኑ ባሻገር በአካባቢው የነበረውን መጥፎ ሽታና ቆሻሻ እንዲጠፋ በማድረግ ጤናማ አካባቢ እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ የደንገል ልማቱ ለስራ ፈላጊዎችም ቢሆን የስራ መስክ እንዲፈጠር ረድቷል፡፡ እንዲሁም በጣና ዙሪያ የተተከለው ደንገል ለጣና ሥነ ምህዳር መጠበቅ ጉልህ ድርሻ እንደሚያበረክት ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው እናቶችና የሕግ ታራሚዎች በፕሮጀክቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ስልጠና በመስጠት እንደአንድ የገቢ ምንጭ በመሆን እገዛ እያደረገላቸው ነው፡፡ የቆቃ ግድብን ከደለል ለመከላከል ሲባል የደንገል ፕሮጀክትን በማስፋፋት በግድቡ ዙሪያ እየተተከለ ይገኛል፡፡ የጽ/ቤቱ አላማም ማህበረሰቡን ያቀፈ ስራ መስራት በመሆኑ ወደፊትም የማህበረሰብ አገልግሎቶችን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ታውቋል፡፡

# እንግዳችን ...

ከገጽ 8 የዞረ

ዩኒቨርሲቲ ሰው የለውም ወይ የተባለበት ጊዜ አለ፡፡ መኪና ከአለቆች ቤት ሊገባ ይችላል፡፡ ነገር ግን ከማንም ግለሰብ ቤት እና ማድቤት የመንግስት መኪና የሚያድርበት ጊዜ አለ፡፡ ይህንን ሳይ ምነው ቶሎ ጡረታ በወጣሁ እላለሁ፡፡ የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር እዚህ ላይ ትኩረት ቢሰጥ እላለሁ፡፡ የመንግስት ንብረት ተይዞ ሰዓት እላፊ እንኳን ቢገባ ህጋዊ ከሆነ ቦታ እና ከመንግስት ቢሮ ነው ማደር ያለበት፡፡

ናይል፡- እንደዚህ እንዳይሆን ከሰዎች ምን ይጠበቃል?

ጉሼ፡- መሆን ያለበት የየግቢው ስምሪት መኪናዎቹን ጠበቅ አድርጐ መያዝና የሚገቡበትንና የሚወጡበትን ሰዓት መቆጣጠር አለበት ብዬ አምናለሁ፡፡ ለወደፊት እርማት ቢሰጠው የምለው ደግሞ «ዩኒቨርሲቲው ጌታ ያጣ ቤት እንዳይሆን» የሚመለከታቸው አካላት የመንግስት ንብረት ማንም ሲፈነጭበት ዝም ብሎ ማየት የለባቸውም፡፡

ናይል፡- ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ስለሆኑ በዝግጅት ክፍላችን ሥም በጣም እናመሰግናለን

ጉሼ፡- እኔም ካሉት ሠራተኞች መርጣችሁ እንግዳ በማድረጋችሁ አመሰግናለሁ፡

# 7ኛው አመታዊ የምስራቅ አፍሪካ

ከገጽ 4 የዞረ

ዶ/ር አቻምየለህ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በመርኃ ግብሩ ላይ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ማተቤ ታፈረ ዩኒቨርሲቲው የያዘውን ራዕይ ለማሳካት ዘጠኝ የምርምር ማዕከላትን ከበቂ ሰው ሃይልና በጀት ጋር በማቋቋም እየሰራ እንደሚገኝ ገልፀው ለአህጉራትና ለአለም አቀፍ ግንኙነቶች፣ ለምርምርና ለማህበረሰብ አገልግሎት እንዲሁም በመማር ማስተማሩ ዘርፍ ለሁለተኛና ሶስተኛ ዲግሪ መርኃ ግብሮች ልዩ ትኩረት በመስጠት እየሰራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡ በሁሉም የባሕር ዳር ከተማ አቅጣጫ ዘጠኝ ግቢዎች ያሉት እንደሆነና ከተማዋን የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከተማ እያደረጋት እንደሆነ ዶ/ር ማተቤ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በዚህ ጉባኤ ላይ የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ከአገራቸው ነባራዊ ሁኔታ ጋር አዛምደው የሚያቀርቡት ምርምር በመሆኑ ልምድ የሚገኝበትና ችግሮቻችንን እንድናይና መፍትሄ እንድንፈልግለት እንዲሁም ለፖሊሲ አውጭዎች ደግሞ እንደ ግብዓት እንደሚያገለግል የገለፁት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአካባቢ ጥበቃና የመሬት አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ አቶ ባይህ ጥሩነህ ናቸው፡፡ አያይዘውም አብዛኛው የምስራቅ አፍሪካ አገሮች በቅኝ ግዛት ሥር የነበሩ በመሆናቸው ከኛ የተሻለ የመሬት አስተዳድርና አያያዝ ልምድ ያላቸው እንደሆነ አቶ ባይህ ጠቅሰው ከዚህ ልምድ የምናገኝበት መድረክ ነው ብለዋል፡፡

የጉባኤው ተካፋዮች ለአንድ አመት የሚያገለግሉ የአመራር አካላትን በመምረጥ ዶ/ር ዳንኤል ወ/ገብርኤል ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሰብሳቢና ፕሮፌሰር ኪያሎ ኪማ ከናይሮቢ ቴክኒካል ዩኒቨርሲቲ ዋና ፀሐፊ በማድረግ ጉባኤው ተጠናቋል፡፡

በጉባዔው ኢትዮጵያን ጨምሮ ከስድስት የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት የተወከሉ 16 ዩኒቨርስቲዎች እና የምርምር ተቋማት እንዲሁም ከ50 በላይ ምሁራን የተሳተፉ ሲሆን የተለያዩ ጥናታዊ ጽሁፎች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡ በመሬት አስተዳደር ተቋም አስተናጋጅነት የተደረገው የዘንድሮው አመታዊ ጉባኤ ከኢትዩላንድኔት (ETHIOLANDNET} ጋር የተቀናጀ ሲሆን ወጪውም በአፍሪካ ህብረት ላንድ ፖሊሲ ኢኒሼቲቭ (Land Policy initiative) እና በዩኤስኤድ (USAID Land Project) ተሸፍኗል፡፡

# ውድቅት (አጭር ልቦለድ)

በደስታ ተከስተ
ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፀጥታ አገልግሎት
ደስታተከስተ4@gmail.com

ጊዜው ውድቅት ሌሊት ሆኗል፡፡ ከእንቅልፍ ምን እንዳነቃው አያውቅም ብቻ አንዳች የሆነ መንፈስ አባኖታል፡፡ መብራቱን አጥፍቶ በጣቱ አማትቦ ፊቱን ተሸፋፍኖ ቢተኛም በድጋሜ እንቅልፍ ሊመጣለት አልቻለም ቁጥሮችን እየደጋገመ በልቦናው ቢቆጥርም የተመኘው እንቅልፍ ፈፅሞ በአይኑ ላይ ሊዞር አልቻለም፡፡
በአይምሮው ውስጥ የማይመላለስ የሀሳብ ባዘቶ አልነበረም፡፡ ከልጅነቱ ጀምሮ አሁን እስከ የሚገኝበት የኑሮ ደረጃ ድረስ ያሳለፈውን የሕይወት ውጣ ውረድ በየምዕራፍ እየከፋፈለ በሀሳቡ … ይተርከው ጀመር…. አንድ ጥሩ ደራሲ አውቆት ቢፅፈው አስገራሚ ታሪክ ያለው መፅሀፍ እንደሚወጣው ታውቆታል፡፡ በእርግጥ እራሱም ቢሆን የስነ-ፅሁፍ ዝንባሌ አለው፡፡ ይህን ተሰጥኦውን ተጠቅሞ እስካሁን የጻፋቸውን አጫጭር የልብ-ወለድ ታሪኮችን ለህትመት ባ ለ መ ብ ቃ ታ ቸ ው ይቆጫል «መፃፍ ብቻ ምን ዋጋ አለው … የተፃፈው ጉዳይ ከሳጥን ወጥቶ ለአንባቢ ካልደረሰ» ይላል ለራሱ ሲታሰበው፡፡

የልጅነት ምኞቱ ታላቅ ደራሲ መሆን ነበር፡፡ ይህን ዝንባሌውን የሚረዱለት የቅርብ ጓደኞቹና የሥራ ባልደረቦቹ «ለምን ሙሉ ጊዜውን በስነ-ፅሁፍ ላይ እንደማያውል» ሲጠይቁት «እስቲ ተውን በታዳጊ ሀገር የሚኖር ሰው … መክሊቱን ሳይሆን ሆዱን ነው የሚከተል፡፡ ስለንባብ ጥቅም ተረድቶ ማንበብ ባሕሉ ያላደረገ ማሕበረሰብ ውስጥ እየኖሩ .. መተዳደሪያን ስነ-ፅሁፍ ማድረግ ቂልነት ነው» እያለ የግሉን አመለካከት ያንፀባርቃል፡፡

በትናንትናው እለት ያጋጠመውን ጉዳይ አስታውሶ ለግል ጉዳዩ የመስሪያ ቤቱን ኃላፊ ሲያነጋግር አስቦ ወደ ቢሮው ይሄዳል፡፡ ፀኃፊዋን ሲያናግራት ለጊዜው ኃላፊው ወጣ እንዳለና እስኪመለስ እርሷ ቢሮ ተቀምጦ እንዲጠብቅ ወንበር እያመላከተች አናገረችው፡፡ እርሱ ግን አመስግኗት ተቀምጦ ከፀሐፊዋ ጋር በቅጽበት ስለሚግባቡ የተወሰኑ ሀሳቦችን ሲለዋወጡ ቆይተው….. “አንዳርጌ….» አለችው ፈገግ እያለች «እባክህ አንተ ከእኔ ስለምትሻል ያሳለፍኩትን የፍቅር ታሪኬን ሳጫውትህና በደንብ ፅፈኸው በፍቅር መፅሄት ላይ እንዲወጣ ብታደርግልኝ … ደስ ይለኝ ነበር ለሌሎች ሰዎች አስተማሪ ይሆናል ብዬ ስለማምን ነው» ስትለው የምትቀልድበት ስለመሰለው «ይቻላል ብዕሩም እውቀቱም በእጃችን ነው … ብቻ አደራሽን ከአለቃሽ ጋር ሆናችሁ ያሳለፋችኋቸውን የእነዚያን ውብ ጊዜአቶች ገጠመኞችሽን ምንም ሳትደብቂኝ እንድታጫውችኝ፡፡ ታሪኬም በአንባቢያን ዘንድ ታማኒነት እንዲኖረው አብራችሁ በመሆን የተነሳችኋቸው ፎቶ ግራፎች ያስፈልጉኛል» በማለት ሲሸረድዳት «እንዴ …. እንዴት …. ምን ለማለት ፈልገህ ነው አንተ?» እያለች አፈጠጠችበት «እና እኔ ምን ሳድርግ የመስሪያ ቤታችን ሰዎች ሲያሙሽ ሰምቼ እኮ ነው» አላት ለመሳቅ እየሞከረ፡፡

ፀሐፊዋ በፊቷ ላይ የንዴትና የቁጣ ገፅታ እየታየባት «ለነገሩ ተዋቸው ምድረ ሀሜተኛ ሁላ ድሮስ እዚህ መስሪያ ቤት ውስጥ የሚሰሩ ሴቶች በየቢሮው እየዞሩ ሰው መቦጨቅ እንጂ …. መቼ የመንግስት ሥራ ይሰሩና ነው…… ቆይ ደግሞ የኔን ስም የምታጠፋው ይች አሮጊት ናት….» አለች «ማናት ደግሞ አሮጊቷ…..» አላት እየተገረመ «ያች ተላላኪዋ ናታ…. እሷማ ወይ አታምር ወይ አትማር ኮሪደር ለኮሪደር እየተመላለሰች እድሜዋን ፈጀችው…. ሀሜተኛ….» አለችው፡፡

«እንዴ….. ወ/ሮ ምትኬን ነው» ሲል «ኧረ ምትክ ይንሳት ይች ነገረኛ….» አለች «ተጣልታችኋል እንዴ? እሷ ሴትዮ ታሳዝነኛለች በዚህች ደሞወዟ አባት የሌላቸውን ልጆች ታሳድጋለች ሲላት «አይምሰልህ ምንም የሚታዘንላት አይደለችም…. ማሽንክ…. ነገረኛ ነች» «ተይ እንጂ እንደዚህ ማለት የለብሽም አንቺም እኮ ሴት ነሽ ….. ነገ ምን እንደሚገጥምሽ አይታወቅም» ሲላት «ይገርምሃል በቀደም ሻይ ቤት ቁጭ ብዬ ስታየኝ በአሽሙር…. ምን ስትል ሰማኋት መሰለህ… ምን የዚህ መስሪያ ቤት ፀሐፊዎች ለስሙ ኮምፒውተር ፊት ለፊት ይጐለቱና ሥራ አይሰሩም ፌስ ቡክ ነው ሲጐረጉሩ የሚውሉት…. አያውቁም እንጂ የፌስ ቡክ ባልና የፎርጅድ ማስረጃ ብዙም አያዋጣ…» እያለች ስታሽሟጥጥ በጣም ነው ያናደደችኝ… አታውቅም እንጂ እኔኮ እዚህ መስሪያ ቤት የተቀጠርኩት ችሎታዬ ተፈትኖ እንጂ እንደሌሎቹ ….» እያለች በመናደድ ጭምር ነገረችው፡፡

ምን የዚህ መስሪያ ቤት ፀሐፊዎች ለስሙ ኮምፒውተር ፊት ለፊት ይጐለቱና ሥራ አይሰሩም ፌስ ቡክ ነው ሲጐረጉሩ የሚውሉት…. አያውቁም እንጂ የፌስ ቡክ ባልና የፎርጅድ ማስረጃ ብዙም አያዋጣ…

አንዳርጌም እንቅልፍ ባጣ አይምሮው ይህን ሲያስታውስ ቆይቶ ድንገት «መስሪያ ቤትና ሀሜተኞች» በሚል ርዕስ ተመርኩዞ ወግ ሊፅፍ አስቦ….. አዎ መጻፍ አለበት በጉዳዩ ዙሪያ ብዙ ማለት ይችላል…. በአይምሮ ውስጥ ሀሳቡ ተግተልትሎ መጣ፡፡ «ተነሳና ጻፍ ጻፍ» የሚል ሀይል ገፋው …. ወዲያው ቀስ ብሎ በትራስጌው በኩል ያለውን ግድግዳ በመዳሰስ የኤሌትሪክ ማብሪያና ማጥፊያውን ሲጫነው «ቀጭ የሚል ድምፅ ተሰምቶ በቅፅበት የመኝታ ክፍሉ በደማቅ ብርሃን ተሞላ፡፡

በእንቅልፍ ላይ ያለችው ባለቤቱን እንዳይረብሻት እየተጠነቀቀ የሌሊት ቁታውን እንደለበሰ ነጠላ ጫማውን ተጫምቶ ነጭ ጋቢውን በትክሻው ላይ ጣል አድርጐ በቀስታ እየተራመደ ወደ ሳሎን ክፍሉ አመራ፡፡

እንደዚህ የመፃፍ ዛሩ እንደተነቃቃ በውስጡ ያለውን ሀሳብ በብዕሩ ሊያቆረቁረው ተጣድፏል፡፡ ወረቀትና ብዕር ከተቀመጠበት አንስቶ በወንበሩ ላይ ተመቻችቶ በመቀመጥ ብዕሩን በጣቶቹ መሀል ሰክቶ በመፃፍ ሊያጐነብስ ድንገት ከፍ ያለ … ከሆድ ውስጥ የወጣ ድምፅ ተሰማው …. ዘወር ሲል ከግድግዳው ጥግ ወለል ላይ እጥፍ ብላ የተኛችውን የቤት ሠራተኛዋን ተመለከታት፡፡ ከላይ የደረበችው አንሶላና ብርደ ልብስ ተሸራቶ በከፊል እርቃኗን ሆና እንቅልፏን ትለጥጣለች «ሚስኪን ለካስ እንቅልፍና ሞት አንድ ነው» የሚሉት አባባል እውነት አለው አለ በልቡ፡፡

የ ጨ በ ጠ ው ን እስኪብርቶ በወረቀቱ ላይ ጣል አድርጐ የሰራተኛዋን የተገለጠ ገላዋን ለማልበስ ተነሳ፡፡ አጠገቧ እንደደረሰም ቆሞ ቁልቁል ሲመለከታት አይኖቹ ከሚያዩት ነገር ላይ ቶሎ ሊመለሱለት አልቻሉም፡፡

በጀርባዋ ተንጋላ የተኛችው ወጣት ሰራተኛ ትንፋሽ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ይሰማዋል በትከሻዋ ላይ ግራና ቀኝ የተዘናፈለው ጥቁር ፀጉሯ ገርበብ ባሉት ከናፍሮቿ መሀል የፈገግታ ያህል ብልጭ ብለው የሚታዩት ጥርሶቿ በእንቅልፍ አለም ውስጥ ሆና ቢሆንም ልዩ ውበት አላብሷታል፡፡ ዝቅ ብሎ ያለውን ከፊል እርቃን ጭኗን ሲመለከት ድንገት የወንድነት ስሜቱ ተነቃቃበት፡፡…. ለሁለት አመት ያህል በቤታቸው ውስጥ ስትኖር ለአንድ ቀንም እንኳን አትኩሮ አይቷት የማያውቀው ሰው …. አሁን በደንብ እየተመለከታት ነው፡፡ ጠቅላላ ሀሳቡና ምኞቱ በእርሷ ሁኔታ ላይ ስለነበረ በምኞት ፈረስ ጋለበባት «ቆንጆ ናት» ሲል ተናገረ ለራሱ ድምፅ ማውጣቱ አልታወቀውም ነበር፡፡ የሚያስተውለው ውበት ብዕር ከሚገልፀው በላይ ሆኖ ነበር…. እንደምንም የውስጥ ስሜቱን እየታገለ ወደ ጤነኛ ሀሳቡ ሲመለስ በቆመበት ደቂቃዎችን እንዳሳለፈ ታወቀው «እንዴ ምን ነካኝ ኧረ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ» አለና በልቡ ተሳቀቀ ለብርድ የተጋለጠውን የሰራተኛዋን ገላ ለማልበስ ከወገቡ ጐንበስ ከማለቱ… አንዳች የተወረወረ ነገር ማሐል አናቱ ላይ ሲያርፍ ተሰማው …. ቁልቁል በአፍጢሙ ሲደፋ «ልክስክስ ወራዳ ባለጌ…» የሚል ቀጭን ድምፅ ከሰራተኛዋ የድንጋጤ ጩኸት ጋር ተቀላቅሎ ለመጨረሻ ጊዜ ተሰምቶታል፡፡ …. የሚወዳት የባለቤቱ የትዕግስት ድምፅ ነበር …..

## ሂሳብን አዝናኝና ተግባር ተኮር …

ከገጽ 4 የዞረ

ምሰሶ ደግፈው ከሚይዙ መሠረታዊ እውቀቶች መካከል ሂሳብ ዋነኛው ነው ብለዋል፡፡ ይህንንም ግምት ውስጥ በማስገባት በሀገራችን ለሂሳብና ለሳይንስ ትምህርቶች በየደረጃው ትኩረት በመስጠት የተለያዩ የውድድር መድረኮች እየተከናወኑ ቢገኙም አሁንም የሂሳብ ጠቀሜታ በበቂ ሁኔታ ያለመረዳት ችግር በብዙ ተማሪዎች ላይ እንደሚስተዋል ዶ/ር ጉርጁ ተናግረዋል፡፡ የት/ክፍሉም ከምርምርና ማሕበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ጋር በመተባበር ግንዛቤ ለመፍጠር የበኩሉን አስተዋፅኦ እየተወጣ ይገኛል፡፡

በዚህ ስልጠና በባሕር ዳር ከተማ ከሚገኙ 21 አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ እንዲሁም የመሰናዶ ት/ቤቶች የተውጣጡ 84 ተማሪዎች፣ 6 የተማሪዎቹ መምህራን፣ 6 ከደብረታቦር፣ ደብረማርቆስና ጐንደር ዩኒቨርሲቲዎች የመጡ መምህራን፣ 6 ከውጭ የመጡ በጐ አድራጊዎች፣ 3 የትምህርትና ስነ ባሕሪ ፋኩልቲ መምህራን እንዲሁም 22 የት/ት ክፍሉ መምህራን ተሳትፈዋል፡፡ ስልጠናው በት/ክፍሉና ከውጭ በመጡ መምህራን አማካኝነት ለተከታታይ ሰባት ቀናት ተሰጥቷል፡፡

## የተማሪዎች ፈጠራ …

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ሀሳብ በገባቸው መጠንና በራሳቸው ተነሳሽነት እንዲሁም ከማዕከሉ በሚያገኙት ስልጠናና ግብአት በመጠቀም በፀሐይ ብርሃን የሚሰራ ማብሰያ (solar Cooker)፣ የውሃ ፓምፕ፣ በሪሞት የሚሰራ ጀልባ (ሕገወጥ የሰዎችን ዝውውር እንዲሁም ኮንትሮባንድን የሚከላከል ቴክኖሎጂ)፣ በአልኮል እንዲሁም በኤሌክትሪክ ሀይል የሚሰራ ሮኬት እና የመሳሰሉትን ሰርተዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዝዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው በጉብኝቱ ለተሳተፉት እንደተናገሩት ተማሪዎቹ ከማዕከሉ ያገኙትን እውቀት ለሌሎች ስልጠናውን ላላገኙት እንዲያካፍሉና ወላጆችም ልጆቻቸው ያገኙትን እውቀት እንዲተገብሩት እገዛ እንዲያደርጉ እንዲሁም ወደ ማዕከሉ እንዲልኩ አደራ ብለዋል፡፡ ዶ/ር ተስፋዬ አያይዘውም የፈጠራ ስራ ለሚሠሩ ተማሪዎች ማዕከሉ እውቀት እና ሽልማት የሚሰጥ መሆኑን ተናግረው ዩኒቨርሲቲው የተቻለውን እንደሚያደርግና ስፖንሰር በማፈላለግ የትምህርት እድል እንዲያገኙ እንደሚያመቻች ለተማሪዎቹ ገልፀዋል፡፡

የማበልፀጊያ ማዕከሉ ዳይሬክተር አቶ ብሬ ጌቴ ማዕከሉ የፈጠራ ስራዎችን ለማሳደግ፣ የሕብረተሰቡን ችግር የሚፈቱ ፈጠራዎችን በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ በኢንጂነሪንግ፣ በሒሳብ፣ በICT እና በሌሎችም የት/ት ዘርፎች በአለም አቀፍ ደረጃ ብቁ እና ተወዳዳሪ ተማሪዎችን ለማፍራት እየሰራ ነው ብለዋል፡፡

በጉብኝቱ ላይ የተገኙት የተማሪዎች ወላጆች ባዩት ነገር በጣም መደሰታቸውንና ልጆቻቸው የፈጠራ ባለሙያዎችና ተመራማሪዎች እንዲሆኑ አቅማቸው በፈቀደ መጠን እገዛ እንደሚያደርጉ ቃል ገብተዋል፡፡ ተማሪዎቹ አሁን ባሳዩት ነገር ሳያቆሙ ወደፊትም አጠናክረው እንዲቀጥሉና ለቀጣዩ ትውልድ እንዲያስተላልፉ እንዲሁም ለሌሎች ተማሪዎች የእነሱን ተሞክሮ ለማስተላለፍ እንዲረዳ የመረጃ ቋት ቢዘጋጅ እና የዩኒቨርሲቲው መምህራን የበለጠ ቢያግዟቸው የበለጠ ውጤታማ እንደሚሆኑ ጠቁመዋል፡፡

የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት በባሕር ዳር ከተማ ድልችቦ ት/ቤት ውስጥ ያስገነባው ይህ ማዕከል ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ አገልግሎት በመስጠት ላይ ሲገኝ ለአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ እንዲሁም ለመሰናዶ ት/ቤት ተማሪዎች እና ለመምህራን አገልግሎት ይሰጣል፡፡

# ከፎቶ ማህደር



The celebration of Nigeria Day at BDU marked the strong and historic diplomatic ties between Ethiopia and the Nigeria, and people to people relationship of the two countries



BDU's graduation ceremony, 2015

ብራና ማተሚያ ቤት ታተመ